1541

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ቀን/Date: ሚያዚያ 29 2016
ቁጥር/Ref. No.: ጠሚ30-2/23

ለፍትህ ሚኒስቴር

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት 30ኛ መደበኛ ስብሰባ የጸደቀ መሆኑን ስለማስታወቅ፣</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚያዚያ 8 ቀን 2016 ዓ.ም ባካሄደው 30ኛ መደበኛ ስብሰባ በሽግግር ፍትሕ ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ተወያይቶ ግብዓቶችን በማከል ውሳኔ ቁጥር 6/መ30/ው135/2016 ሆኖ ስራ ላይ እንዲውል አጽድቋል።

ስለሆነም ምክር ቤቱ በሰጣቸው ግብዓቶች መሰረት የተስተካከለውን የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ አንድ ቅጂ በዚህ ደብዳቤ ሸኚነት መላካችንን እየገለጽን ፖሊሲው ስራ ላይ እንዲውል እናስታውቃለን።

ከሠላምታ ጋር

አ... ፀሐይ ጳውሎስ አትሞ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊና
የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
Office of the Prime Minister

<u>ግልባጭ</u>

- ለካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር ጼኤታ
- ለህግ ጉዳዮች መሪ ሥራ አስፈጻሚ

<u>ጠ/ሚ/ጽ/ቤት</u>

ስልክ/Tel.: +251 111 241 214
ፋክስ/Fax: 226 292
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box: 1031

ኢትዮጵያ፡ አዲሲቷ የተስፋ አድማስ
Ethiopia: A New Horizon of Hope
@PMEthiopia @PMoEthiopia

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ

በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀ

መጋቢት 2016 ዓ.ም

ማውጫ

I..................................................................................................................................መግቢያ
..................................................................................................................................3

II. የቃላት እና የሀረጋት ፍቺ ..................................................................................4

ክፍል አንድ ..................................................................................................................6

ጠቅላላ ..........................................................................................................................6

1.1. ስያሜ 6

1.2. የፖሊሲው መነሻ ሁኔታዎች እና አስፈላጊነት ..................................................6

1.3. ፖሊሲውን የማውጣት ስልጣን ..........................................................................7

1.4. የፖሊሲው ዓላማ ..................................................................................................7

1.5. ፖሊሲው የሚመራባቸው መርሆዎች ....................................................................7

1.6. የተፈፃሚነት ወሰን ..................................................................................................8

ክፍል ሁለት ..................................................................................................................9

የፖሊሲ ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች ..........................................................................9

2.1. የወንጀል ተጠያቂነት ..............................................................................................9

2.1.1. ምርመራና ክስ የሚከናወንባቸው ወንጀሎች ..................................................9

2.1.2. ምርመራና ክስ የሚከናወንባቸው አጥፊዎች ....................................................10

2.1.3. የወንጀል ምርመራ እና ክስ የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት ..........................11

2.1.4. የፍርድ ሂደት የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት ..................................................12

2.2. እውነትን ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና የዕርቅ ተግባር ......................................13

2.2.1. እውነትን ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና ዕርቅ ተግባራዊ የሚደረግባቸው ጉዳዮች ......13

2.2.2. እውነትን የማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና የዕርቅ ተግባራት የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት ......14

2.3. በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረት ..........................................................15

2.3.1. ለምህረት ብቁ የማያደርጉ ሁኔታዎች ..............................................................15

2.3.2. ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ..............................................................15

2.3.3. የምህረት ተግባር የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት ..........................................16

2.4. ማካካሻ ....................................................................................................................16

2.4.1. ተግባራዊ የሚደረጉ የማካካሻ ዓይነቶች እና ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች ..............16

2.4.2. ማካካሻ የሚመራበት ተቋማዊ ሥርዓት ..........................................................17

2.5. ተቋማዊ ማሻሻያ ....................................................................................................17

2.5.1. የተቋማዊ ማሻሻያ ስራ ትኩረት የሚያደርግባቸው ተቋማት ....18
2.5.2. የተቋማዊ ማሻሻያ ስራ የሚመራበት ተቋማዊ ሥርዓት ....19
2.6. የሽግግር ፍትሕ ተግባራዊ የሚደረግበት የጊዜ ወሰን ....20
2.7. በሽግግር ፍትሕ ትግበራ የክልሎች ሚና ....20
2.8. በሽግግር ፍትሕ የባህላዊ የፍትሕ ሥርዓቶች ሚና ....21
2.9. የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች (cross-cutting issues) ....22
ክፍል ሦስት ....23
የመንግስት እና የባለድርሻ አካላት ሚና እና የክትትል እና ድጋፍ ሥርዓት ....23
3.1. የመንግስት አካላት እና ባለድርሻ አካላት ሚና ....23
3.1.1. የመንግስት አካላት ሚና ....23
3.1.2. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሚና ....26
3.2. የፖሊሲው አፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ....28



Federal Democratic Republic of Ethiopia
Office of the Prime Minister

## I. መግቢያ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት አገሪቱ በተቀበለቻቸው ዓለም-አቀፋዊ እና አህጉራዊ ስምምነቶች እንዲሁም በህገ መንግስቱ የተጣሉበትን የዜጎችን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የማክበር እና የማስከበር ኃላፊነቱን ለመወጣት፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማስፋፋት እና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን እውን ለማድረግ የተለያዩ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፥ ሕጎችን እና የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅዶችን በማውጣት ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በዚህ ረገድ በተለይ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ የተከሰተውን የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ መንግስት ለአለመግባባት፣ ለግጭት፣ ለሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና ለተለያዩ የህዝብ ጥያቄዎች መፍትሔ ይሰጣሉ፣ የሰብአዊ መብት አያያዝን ያሻሽላሉ፣ የፍትሕ እና መልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፣ ለግጭት እና አለመግባባት መነሻ ለሆኑ መሰረታዊ ችግሮች መፍትሔ ይሆናሉ፣ በአጠቃላይም የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ፣ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታን ለማፋጠን፣ ፍትሐዊ የሆነ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ልማትን እና አሳታፊና አካታች ፖለቲካዊ ሥርዓትን ለመገንባት ያስችላሉ ያላቸውን ዘርፈ ብዙ የህግ እና ተቋማዊ ማሻሻያ ስራዎችን ተግባራዊ አድርጓል፡፡

ይሁን እንጂ ባለፉት አመታት እና ከዚያም ቀደም ብሉ ባለፉት ዘመናት በበርካታ የአገሪቱ አካባቢዎች በተፈጠሩ አለመግባባቶች፣ ቅራኔዎች፣ ከባድ ግጭቶች እና  የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በርካታ ዜጎች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፤ ለንብረት ውድመት፣ ለአካል ጉዳት እና ለሞት ተዳርገዋል፤ በብዙ የአገሪቱ ክፍሎች ለዘመናት የዳበሩ የአብሮነት እና የመቻቻል እሴቶች ላልተዋል፡፡ በጥቅሉ በየጊዜው የሚነሱ አለመግባባቶች፣ ጦርነቶች፣  ግጭቶች እና ጉልህ የሰብዓዊ  መብት ጥሰቶች አገሪቱን ለከፋ አደጋ የዳረጉበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

በአገሪቱ በተለያዩ ዘመናት የተከሰቱ እና የቀጠሉ ተደራራቢ እና ሰፊ የተጎጂና የአጥፊ ወሰን ያላቸው የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፣ የእርስ በእርስ ግጭቶች፣ ያልጠሩ ትርክቶች እና በደሎችን ለመፍታት የተለያዩ ሙከራዎች ተደርገዋል ፡፡ ሆኖም እነዚህ አሰራሮች በእውነት፣ በዕርቅ፣ በምህረት እና በፍትሕ ላይ የተዋቀረ እና በግልፅ ፖሊሲ የሚመራ ሁለተናዊ የሽግግር ፍትሕ ስልትን አካታች፣ ሰብአዊ መብት—ተኮር በሆነ እና በተሰናሰለ መንገድ ባለመተግበራቸው የሚፈለገውን ዘላቂ መፍትሔ ማምጣት አልቻሉም።

ስለሆነም ለችግሮች እና አገራዊ ፈተናዎች ስር-ነቀል እልባት ከመስጠት አንፃር ከነበሩ አገራዊ ሙከራዎች እና የሌሎች አገራት መልካም ተሞክሮዎች በመማር፣ አግባብነት ያላቸው የዓለም-አቀፍ ሰነዶች ስለሽግግር ፍትሕ አካሄድ ያስቀመጧቸውን ደረጃዎች ግምት ውስጥ በማስገባት የተሟላ የሽግግር ፍትሕ ሂደትን በአገሪቱ በመተግበር በየጊዜው ከሚከሰቱ ችግሮች መውጣት እና ዘላቂ ሰላም እና ፍትሕን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

በ2011 ዓ.ም በአዲስ አበባ የፀደቀው የአፍሪካ ኅብረት የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ማዕቀፍ የሽግግር ፍትሕ  ሀገራት የተለያዩ የፖሊሲ እርምጃዎችን እና ተቋማዊ አሠራሮችን በመጠቀም ያለፉ ጥሰቶችን፣ ክፍፍሎችን እና አለመመጣጠኖችን ለማስወገድ እና ለደኅንነት፣ ለዴሞክራሲ፣ ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ሥርዓት ግንባታ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚደረግ  አስፈላጊ ሂደት እንደሆነ ይገልጻል። ከተለያዩ አገራት ልምድ እንደታየውም የሽግግር ፍትሕ ሥርዓት ከእርስ በእርስ ጦርነት፣ ግጭት እና ጭቆና በመውጣት በፖለቲካ እና ዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ትርጉም ያለው ሽግግር ለማድረግ በሞከሩ በርካታ ሀገራት ተተግብሯል፤ በዕውነት፣ ዕርቅ እና ፍትሕ ላይ የተመሰረተ ዘላቂ ሰላም በማስገኘት ረገድም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል።

በአገሪቱ ለዘመናት የተፈጸሙ እና አሁንም የቀጠሉ ያልጠሩ ትርክቶች፣ ቁርሾዎች፣ አለመተማመኖች፣ የእርስ በእርስ ግጭቶች፣ የሰላም እጦቶች፣ አለመረጋጋቶች እና እነዚህን አስታከው የሚፈጸሙ ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በስፋት ከመኖራቸው ጋር ተያይዞ ለችግሮቹ ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት እና ሁሉን አቀፍ ፍትሕ ለማስፈን አገሪቱ በተሟላ የሽግግር ፍትሕ ሂደት እንድታልፍ ማድረግ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ስለመሆኑ በገለልተኛ የባለሙያዎች ቡድን የተደረገ ጥናት አረጋግጧል። በተመሳሳይ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ከተቀሰቀሰው ጦርነት ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽን ጽሕፈት ቤት ባወጡት ጣምራ የምርመራ ውጤት ላይ በግጭቱ ማእቀፍ የተፈጸሙ ወንጀሎችና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በሽግግር ፍትሕ ማእቀፍ ሊታዩ እንደሚገባ ምክረ ሀሳብ ቀርቧል፡፡ ከዚህ ባለፈም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ከነበረው ጦርነት ጋር ተያይዞ በፌዴራል መንግስት እና በህዝባዊ ወያነ ሀርነት ትግራይ (ህወሀት) መካከል በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ በተፈረመው የሰላም ስምምነት ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ የተፈፀሙ ወንጀሎችና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በሽግግር ፍትሕ ሂደት ሊፈቱ እንደሚገባ ተመላክቷል፡፡

ከዚህ በመነሳት እና በአገር አቀፍ ደረጃ በተደረጉ ሕዝባዊ ምክክሮች የተገኙ ግብዓቶችን ታሳቢ በማድረግ በተለያዩ ጊዜያት በአገሪቱ የተፈጠሩ ውስብስብ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት እንዲቻል አሳታፊ፣ አካታች፣ ከዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብት መርሆዎችና ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣመ፣ መሰረታዊ የሽግግር ፍትሕ መርሆዎችን የተከተለ፣ የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ፣ እንዲሁም አፈፃፀሙን አሳታፊ እና ሰብአዊ መብት ተኮር በሆነ አካሄድ በመምራት እና ስልቶችን በተሰናሰለ መልኩ በመተግበር ዘላቂ ሰላም፣ የሕግ የበላይነት እና ፍትሕን ለማረጋገጥ የሚያስችል የሽግግር ፍትሕ ሂደት በአገር-አቀፍ ደረጃ መተግበር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ወጥቷል።

## II. የቃላት እና የሀረጋት ፍቺ

ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ የሚከተሉት ቃላት/ሀረጎች ቀጥሎ የተመለከተው ፍቺ ይኖራቸዋል፡-

1. **ለዚህ ፖሊሲ የወንጀል ምርመራና ክስ ዓላማ "ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰት"** ማለት ስልታዊ፣ መጠነ-ሰፊ ወይም ተከታታይነት (pattern) ባለው ሁኔታ የተፈጸመ ወንጀል ሲሆን በዋናነትም የሰው ዘር የማጥፋት ወንጀል፣ የጦር ወንጀል፣ በሰብአዊነት ላይ የሚፈፀም ወንጀል፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ ወንጀል፣ አስገድዶ ሰውን የመሰወር ወንጀል፣ ኢ-ሰብአዊ አያያዝ፣ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል እና ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት፣ ሰውን ከመደበኛ የመኖሪያ ቦታ ከሕግ አግባብ ውጭ የማፈናቀል ድርጊት፣ በሕፃናት ላይ የሚፈፀም ወንጀል፣ በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈፀም ወንጀል፣ ብሔርን፣ የፖለቲካ አመለካከትን ወይም ኃይማኖትን መሰረት በማድረግ የሚፈፀም ወንጀል (persecution)፣ ወይም ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም-አቀፍ ስምምነቶች መሰረት ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ ዓለም አቀፍ ወንጀል ህግ ጥሰት ወይም ከባድ የሰብዓዊነት ህግ ጥሰት ተብሎ የተለየ ማንኛውም ሌላ ወንጀልን ያካትታል፤
2. **"ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያለው አጥፊ"** ማለት ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰት በማቀድ፣ በመምራት፣ በማቀነባበር ወይም ትዕዛዝ በመስጠት እንዲፈፀም ያደረገ፣ ከፍተኛ ሀላፊነት ኖሮበት ሀላፊነትን ባለመወጣት ጉዳት እንዲደርስ ያደረገ ወይም በራሱ ተነሳሽነት በቀጥታ የፈፀመ ወይም በሌላ ማንኛውም ሁኔታ በወንጀሉ አፈፃፀም ከፍተኛ ሚና ያለው ሰው ነው፤

3. **"እውነት ማፈላለግ"** ማለት የጉልህ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች፣ በደሎችና ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኢ-ፍትሐዊነቶችን መሠረታዊ ምክንያት፣ ሁነት፣ መጠን እና ዓይነት ተጎጂ-ተኮር በሆነ መንገድ ለማፈላለግ፣ ለመለየት እና ይፋ ለማውጣት የሚረዳ የሽግግር ፍትሕ ስልት ነው፤

4. **ለዚህ ፖሊሲ የእውነት ማፈላለግ ዓላማ "ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰት"** ማለት መጠነ ሰፊ፣ ስልታዊ፣ ወይም ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ፣ ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብት ሕጎችን፣ ዓለም አቀፍ የወንጀል ህግን ወይም የሰብአዊነት ሕግን በመጣስ የሚፈጸም /ጥሰት ሲሆን በወንጀሉ ዓይነት፣ እና በደረሰው የጉዳት መጠን መሰረት ተደርጎ የሚለይ ሌላ ወንጀልን ያካትታል፤

5. **"ዕርቅ"** ማለት በግጭት ወይም ሌላ አውድ በተፈጸሙ በደሎች፣ ጥሰቶች እና ኢ-ፍትሀዊነቶች ምክንያት የተጎዱ ወይም የላሉ ማህበረሰባዊ ግንኙነቶች እና እሴቶች፣ የተፈጠሩ አለመተማመኖች፣ ጥላቻዎች፣ ቅራኔዎች፣ ቁርሾዎች እና መገፋፋቶች መፍትሔ እንዲሰጣቸው በማድረግ ግንኙነቶቹ እና እሴቶቹ የሚጠገኑበት፣ እንዲሁም ጥላቻ፣ አለመተማመን እና መከፋፈል የሚወገድበት አሰራርን የሚመለከት አንድ የሽግግር ፍትሕ ሂደት እና ግብን የሚያመለክት ፅንሰ-ሀሳብ ነው፤

6. **"ማካካሻ"** ማለት ተጎጂዎችን ወደነበረበት መመለስ እና መልሶ ማቋቋም፣ ካሳ፣ የማገገሚያ እርምጃ፣ ፈውስ፣ የመታሰቢያ ወይም የማስታወሻ ክንዋኔ እና ያለመደገም ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚረዱ እርምጃዎችን የሚያካትት ዘርፈ-ብዙ ጉዳዮችን የያዘ የሽግግር ፍትሕ ስልት ነው፤

7. **"ፈውስ"** ማለት ተጎጂዎች ለደረሰባቸው ጉዳት ወይም የሰብዓዊ መብት ጥሰት በተገቢ መልኩ ይፋ የማውጣት፣ ለደረሱ ጥሰቶት እውቅና የመስጠት እና በይፋ ይቅርታ የመጠየቅ፣ ተገቢ የመታሰቢያ እና ማስታወሻ ክንዋኔዎችን የማድረግ እና የቀጠሉ ተመሣሣይ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የማስቆም እርምጃዎችን የሚያካትት ተግባር ነው፤

8. **"ማገገሚያ"** ማለት ተጎጂዎች የደረሰባቸው አካላዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ጉዳት፣ በደል እና ቁስል የሚያገግምበት፣ የሚጠገንበት የሕክምና፣ የሥነ-ልቦና፣ የህግ ድጋፍ እና ሌሎች ለዚህ ዓላማ የሚሰጡ አገልግሎቶችን የሚያካትት የማካካሻ ዓይነት ነው፤

9. **"ተጎጂ"** ማለት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰት የደረሰበት ሲሆን የሕይወት፣ የአካል፣ የሥነ-ልቦና፣ የንብረት ወይም ሌላ ዓይነት ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው ወይም ማህበረሰብን የሚመለከት ነው፤

10. **"ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች"** ማለት ሴቶች፣ህጻናት፣አካል ጉዳተኞች፣አረጋውያን፣የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ሌሎች ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን የሚያካትት ነው፡፡

11. **"ክልል"** ማለት በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 47 መሰረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ነው፤

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ጉዳዮች

### 1.1. ስያሜ

ይህ ፖሊሲ **"የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ"** ተብሎ ይጠራል።

### 1.2. የፖሊሲው መነሻ ሁኔታዎች እና አስፈላጊነት

ኢትዮጵያ የበርካታ ብሄር ብሄረሰቦች መኖሪያ፣ ለዘመናት የቆዩ ጥንታዊ ባህሎች፣ እምነቶች እና ቅርሶች ባለቤት፣ እንዲሁም የአፍሪካውያን የነጻነት እና ብሄራዊ ኩራት መገለጫ አገር ናት። ኢትዮጵያ ባለፉት ዘመናት በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ እና በማህበራዊ ዘርፎች ከፍተኛ እመርታን ማሳየት ብትችልም በተለያዩ ጊዜያት በመንግስት መዋቅሮች እና መንግስታዊ ባልሆኑ ግለሰቦችና ተቋማዊ ተዋንያን የተፈጸሙ ግጭቶች፣ በደሎች እና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተደጋጋሚ ኡደት በአገረ–መንግስቱ የዘላቂ ሰላም ግንባታ፣ የሰብአዊ መብት አጠባበቅ እና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጥረቶች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሲፈጥር ቆይቷል፤ አሁንም እየፈጠረ ይገኛል።

በአገሪቱ በተለያዩ ጊዜያት የተፈፀሙ ከባድ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና ወንጀሎች በተገቢው መንገድ ምላሽ እንዲያገኙ ከማድረግ እና በቀጣይ የማይደገሙበትን ፖለቲካዊ አውድ ከመፍጠር አንፃር በተለያዩ የመንግስት ስርዓቶች ተጠያቂነት፣ ዕርቅ እና ሌሎች የሽግግር ፍትሕ አምዶችን ያካተቱ ውስን ጥረቶች ተደርገዋል። ሆኖም የተወሰዱት እርምጃዎች በዋነኝነት ተጎጂዎችን ያላሳተፉ፣ ግልፀኝነት የጎደላቸው፣ ሁሉ–አቀፍ ያልሆኑ፣ ከሽግግር ፍትሕ ስልቶች ውስጥ በክስ እና ዕርቅ ላይ ብቻ በማተኮር ሌሎች ስልቶችን በተሰናሰለ ሁኔታ ያልተገበሩ ነበሩ። የተደረጉ ተቋማዊ ማሻሻያዎችም ቢሆኑ ዘላቂ ለውጥ እና የተሟላ የተጠያቂነት ስርዓትን ማምጣት ባለመቻላቸው በየዘመኑ የተፈጸሙና የቀጠሉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና የፍትሕ ጥያቄዎችን በዘላቂነት ለመፍታት፣ እንዲሁም የተሟላ ሰላም፣ ፍትሕ እና ዲሞክራሲ ለማስፈን ሳይቻል ቀርቷል።

ማናቸውም የሽግግር ፍትሕ ሥርዓት በዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብት መርሆዎች ላይ የተመሰረተ፣ እንዲሁም ሁሉን–አቀፍ እና አካታች የትግበራ ሂደትን ተከትሎ የሚፈጸም ከሆነ ዘላቂ ሰላም እና ፍትሕ ለማስፈን እና ዲሞክራሲያዊ የአገር ግንባታን ለማሳለጥ ወሳኝ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው የተለያዩ ሀገራት ተጨባጭ ተሞክሮ ያሳያል። መጠነ ሰፊ እና ከባድ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ የሚኖረው ሚና ከፍ ያለ ነው።

በኢትዮጵያም ዘመን ለዋጁ በደሎች ፍትሕን ለማረጋገጥ፣ ቁርሾዎችን ለመቀነስ እና የቀጠሉ ግጭቶች እና የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በዘላቂነት ለማስቆም ከምንጊዜውም በላይ ተጠያቂነትን በማስፈን የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ለተፈጸሙ በደሎች እና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እውነትን ማፈላለግ እና ይፋ ማውጣት፣ በቅድመ–ሁኔታ ላይ የተመሰረተ የምህረት አሰራር መተግበር፣ ግለሰባዊ እና ማህበረሰባዊ ዕርቅን ማሳለጥ፣ የማካካሻ ሥርዓትን መመስረት፣ እንዲሁም የተቋምና የህግ ማሻሻያ ስራዎችን ተግባራዊ በማድረግ በተጎጂዎች ላይ ያተኮረ የተሟላ የሽግግር ፍትሕ ሥርዓት መተግበር ፍፁም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ስለሆነም በኢትዮጵያ የሚተገበረው የሽግግር ፍትሕ ዓላማ እና የአፈፃፀም ሂደቱ ሊከተላቸው የሚገቡ መሰረታዊ መርሆዎችን በግልፅ ለማመልከት፣ በትግበራ ሂደት ለሚወሰዱ የህግ፣ የአሰራር እና የአደረጃጀት እርምጃዎች ተገቢ አቅጣጫ ለማስቀመጥ፣



Federal Democratic Republic of Ethiopia
Office of the Prime Minister

የሽግግር ፍትሕ ትግበራው በዓለም አቀፍ እና አህጉር–አቀፍ ሰነዶች ላይ የተመላከቱ መርሆዎችን በተከተለ አግባብ የሚካሄድበትን አሰራር ለማረጋገጥ፣ በአጠቃላይም ወጥነት ያለው፣ ግልጽ፣ ተጠያቂነት እና ፍትሕን የሚያሰፍን የሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደትን ለመምራት እንዲቻል ይህን የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

### 1.3. ፖሊሲውን የማውጣት ስልጣን

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 51(2) መሰረት የፌዴራል መንግስት በአገር አቀፍ ደረጃ የሚተገበሩ ፖሊሲዎችን ለማውጣት እና አፈፃፀማቸውን ለመከታተል በተሰጠው ስልጣን ማእቀፍ ይህ ፖሊሲ ወጥቷል፡፡

### 1.4. የፖሊሲው ዓላማ

የፖሊሲው አጠቃላይ ዓላማ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አውድ መሰረት ያደረገ፣ የተቀናጀ እና የተናበበ የሽግግር ፍትሕ ሂደት የሚመራበት እና የሚተገበርበትን ሥርዓት በመዘርጋት ዘላቂ ሰላም፣ ዕርቅ፣ የህግ የበላይነት፣ ፍትሕ እና ዲሞክራሲ የሚረጋገጥበትን መደላድል መፍጠር ነው፡፡

ፖሊሲው የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1.4.1. በሽግግር ፍትሕ ማእቀፍ የወንጀል ምርመራ እና ክስ፣ እውነት ማፈላለግ፣ ዕርቅ፣ በቅድመ–ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረት፣ ማካካሻ እና ተቋማዊ ማሻሻያ የሚኖራቸውን ዓላማ፣ ግብ፣ መስተጋብር እና የሚመሩባቸውን መሰረታዊ መርሆዎች እና ተቋማዊ አደረጃጀት በግልጽ ማመላከት፣ ለአተገባበራቸው ተገቢ የሕግ፣ የአሰራር እና የአደረጃጀት አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ፤

1.4.2. የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው የተለያዩ ስልቶች ተፈፃሚ የሚሆኑበትን የጊዜ ወሰን በግልጽ ማስቀመጥ፤

1.4.3. በሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደት ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች የሚኖራቸውን ሚና በግልጽ ማስቀመጥ፤

1.4.4. በሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደት የክልሎችን ተሳትፎ እና ሚና ማመላከት፤

1.4.5. ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች እና ተጎጂዎች በሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደት የሚኖራቸውን ሚና እና ሊደረግላቸው የሚገባውን ልዩ ትኩረት በግልጽ ማስቀመጥ።

### 1.5. ፖሊሲው የሚመራባቸው መርሆዎች

ፖሊሲው በሚከተሉት መርሆዎች ይመራል፡-

1.5.1. **ሰብአዊ መብት ተኮር የትግበራ ሂደት፡-** በሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት በዓለም–አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍ እና አገራዊ የሽግግር ፍትሕን በሚመለከቱ ሰነዶች ላይ የተቀመጡ ህጎችን፣ መርሆዎችንና እሴቶችን ታሳቢ ያደረጉ ይሆናል፤

1.5.2. **ከጥቃት ወይም ከጉዳት መጠበቅ፡-** የሽግግር ፍትሕ ሂደት የማንኛውንም ተሳታፊ እና ተጎጂ ደህንነት በጠበቀ እና ከዳግም ጥቃት ወይም የጉዳት አደጋ የመጠበቅ መብትን በሚያረጋግጥ አግባብ ተግባራዊ ይደረጋል፤

1.5.3. **አገራዊ ባለቤትነት፡-** የሽግግር ፍትሕ ሂደት አገራዊ ባለቤትነትን ባረጋገጠ አግባብ በመንግስት፣ በሕዝብ እና ቀጥተኛ ባለድርሻ አካላት ፍላጎት፣ ሀላፊነት፣ ባለቤትነት እና ውሳኔ ይመራል፤

1.5.4. **አውድ ተኮር የአተገባበር ሥርዓት፡-** የሽግግር ፍትሕ ስርዓቱ አገራዊ እና አካባቢያዊ ነባራዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ባስገባ እና የሁሉንም ማህበረሰብ ክፍሎች የሽግግር ፍትሕ ጥያቄ፣ የጋራ ትልም እና ተስፋን ባማከለ አካሄድ ይተገበራል፤

1.5.5. **ተጠያቂነት፡-** የሽግግር ፍትሕ ሂደት ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ ይመራል፤

1.5.6. **ሁለንተናዊነት፡-** የሽግግር ፍትሕ ሂደት የተለያዩ ስልቶችን በማቀናጀት በተናበበና ተመጋጋቢ በሆነ መልኩ እንደአስፈላጊነቱም ቅደም ተከተልን በጠበቀ አግባብ ይተገበራል፤

1.5.7. **አካታችነትና አሳታፊነት፡-** የሽግግር ፍትሕ ሂደት በፖለቲካ አመለካከት፣ በዘር፣ በቀለም፣በኃይማኖት፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ወይም በሌላ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ልዩነትን ሳያስተናግድ፣ ማንኛውንም አድሏዊ መስፈርት እና አመለካከትን በማስወገድ ግልጽ፣ ሁሉን—አቀፍ፣ አካታች፣ በአገሪቱ ያለውን ብዝሀነት በሚያንፀባርቅ እና ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች እና ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በሚያሳትፍ መንገድ ይተገበራል፤

1.5.8. **ስርዓት-ጾታ ተኮር አተገባበር**፡- የሽግግር ፍትሕ ሂደት ከቅድመ ዝግጅት ክዋኔዎች እስከ ሙሉ አተገባበር ባሉ ምዕራፎች ሁሉ የሴቶች ተመጣጣኝ ውክልና እና ትርጉም ያለው ተሳትፎ የሚረጋገጥበትን አሰራር ይዘረጋል፤

1.5.9. **ልዩ ትኩረት የሚሹ የህበረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ፡-** የሽግግር ፍትሕ ሂደት ትግበራ ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ልዩ ፍላጎት እና ምልከታን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ እንዲሁም በሂደቱ ላይ ያላቸውን ባለቤትነት የሚያረጋግጥ ይሆናል፤

1.5.10. **ቅንጅትና ትብብር**፡- የሽግግር ፍትሕ በህዝብ፣ በመንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት እና ባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር ይተገበራል፤

1.5.11. **አገር በቀል የግጭት አፈታት እሴቶችን ጥቅም ላይ ማዋል፡-** በአገራችን የሚገኙ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች እና እሴቶች እንደአስፈላጊነቱ ተገቢ ማሻሻያዎችን እንዲያካሂዱ በማድረግ በሽግግር ፍትሕ ሂደት ሚና እንዲኖራቸው ይደረጋል።

## 1.6. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ፖሊሲ በመላ አገሪቱ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## የፖሊሲ ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች

### 2.1. የወንጀል ተጠያቂነት

የወንጀል ተጠያቂነት የሽግግር ፍትሕ ሂደት ከሚተገበርባቸው መሰረታዊ የሽግግር ፍትሕ ስልቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ተግባራዊ የሚደረገው የሽግግር ፍትሕ ሂደት የወንጀል ምርመራ በማካሄድ እና ክስ በመመስረት አጥፊዎች ተጠያቂ የሚሆኑበትን ሥርዓት የሚዘረጋ ይሆናል።

በሽግግር ፍትሕ ማዕቀፍ የወንጀል ተጠያቂነትን ማረጋገጥ አገሪቱ ያለባትን ዓለም አቀፍ ግዴታ ለመወጣት፣ የሰዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ፣ ሰላም እና መረጋጋት ለማምጣት፣ የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ እና ተመሳሳይ ወንጀሎች እንዳይደገሙ ለማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው።

ስለሆነም በሽግግር ፍትሕ ሂደት ምርመራ እና ክስ የሚከናወንባቸውን ወንጀሎች እና አጥፊዎች መለየት እንዲሁም የወንጀል ምርመራ፣ የክስ እና የፍርድ ሂደቶችን የሚያከናውኑ አካላትን በፖሊሲው ማዕቀፍ በግልጽ ማመላከት ተገቢ ይሆናል፡፡

#### 2.1.1. ምርመራ እና ክስ የሚከናወንባቸው ወንጀሎች

የወንጀል ተጠያቂነት የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ እና ፍትሕ ለማስፈን የሚያስችል አንዱ የሽግግር ፍትሕ ስልት እንደመሆኑ መጠን በሽግግር ፍትሕ ሂደት ምርመራ የሚካሄድባቸው እና ክስ የሚመሠረትባቸው ወንጀሎችን መወሰን አስፈላጊ ይሆናል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶችን መሰረት ባደረገ መልኩ ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በወንጀል ክስ ሂደት ማለፍ እንደሚኖርባቸው እና በይቅርታም ሆነ በምህረት ሊታለፉ እንደማይገባ በግልጽ አስቀምጧል። በተመሳሳይ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች አገራት በጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ላይ የወንጀል ተጠያቂነትን እንዲያረጋግጡ ያስገድዳሉ፡፡ የአፍሪካ ህብረት የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲም በሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደት የተወሰኑ ወንጀሎች በወንጀል ክስ ሂደት ሊያልፉ እንደሚገባ ያስቀምጣል፡፡

የሽግግር ፍትሕ ዋና ዓላማ እና ግብ የወንጀል ተጠያቂነት ስልትን ብቻ በመጠቀም ሁሉን–አቀፍ ፍትሕ ለማምጣት መሞከር አይደለም፡፡ ሁሉንም የሽግግር ፍትሕ ስልቶች በተቀናጀ እና በተጣጣመ መልኩ በመተግበር ፍትሕ ማስፈን፣ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ እና ዘላቂ ሰላም እና መረጋጋትን ማስፈን ያስፈልጋል፡፡ በአገሪቱ በሚተገበረው የሽግግር ፍትሕ ሂደት በጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ላይ ብቻ ያተኮረ ምርመራና ክስ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

በወንጀል ምርመራና ክስ ሂደቱ የማይካተቱ ጉልህ ያልሆኑ ጥሰቶች ሌሎች የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን በመጠቀም መፍትሔ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ለዚህም የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን በተቀናጀ እና በተጣጣመ መልኩ እንዲተገበሩ ይደረጋል።

ከዚህ አንፃር ከወንጀል ምርመራና ክስ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ በሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደት የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎችና ስልቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-

- ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና ከባድ ወንጀሎችን መለየት የሚያስችል ግልፅ መለያ መስፈርት ይዘረጋል፤

- በአገሪቱ የወንጀል ሕግ ውስጥ ያልተካተቱ ዓለም-አቀፍ ወንጀሎችን በተመለከት ሀገሪቱ ከተቀበለቻቸው ዓለም-አቀፍ ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ አዲስ የሕግ ማዕቀፍ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፤
- የወንጀል ምርመራ እና ክስ ስራዎችን በተሟላ ሁኔታ ለመተግበር የሚያስችሉ የአሰራር ሥርዓቶች ይዘረጋሉ።

### 2.1.2. ምርመራ የሚከናወንባቸው እና ክስ የሚመሰረትባቸው አጥፊዎች

በሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደት የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን በተቀናጀና በተጣጣመ መልኩ መተግበር ፍትሕ ለማስፈን፣ የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ እና ዘላቂ ሰላምና መረጋጋትን ለማምጣት አስፈላጊ እና መሰረታዊ ጉዳይ ነው። ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታዎች አንፃር በሁሉም አጥፊዎች ላይ ምርመራ ማካሄድ እና ክስ መመስረት ተመራጭ አካሄድ አይሆንም።

ከአጥፊዎቹ ብዛት፣ የሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ከሚተገበርበት የጊዜ ወሰን ስፋት፣ በዓለም-አቀፍ ደረጃ ካለው የሽግግር ፍትሕ ተሞክሮ አኳያ፣ እንዲሁም በአጥፊዎች ላይ የወንጀል ምርመራ እና ክስ ስራዎችን ለማካሄድ ከሚያስፈልገው ረጅም ጊዜ እና ከሚጠይቀው ከፍተኛ ወጪ አንፃር የምርመራ እና ክስ የመመስረት ስራው ትኩረት ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ብቻ ይሆናል። በዚህ አግባብ የወንጀል ተጠያቂነትን ማረጋገጥ በሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደት የተሻለ እና የተለመደ አካሄድ ነው።

በጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰትድርጊት የተሳተፉ ነገር ግን ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ የሌላቸው አጥፊዎችን በተመለከተ እንደየአግባብነቱ ሌሎች የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን በመጠቀም ጉዳያቸው የሚታይበትና መፍትሔ የሚሰጥበት ሥርዓት ይዘረጋል።

በሽግግር ፍትሕ ትግበራ የወንጀል ምርመራ የሚካሄድባቸው እና ክስ የሚመሰረትባቸው አጥፊዎችን በተመለከተ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች እና ስልቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-

- በጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰት/ አፈፃፀም ሂደት ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች የሚለዩበት ግልጽ ሥርዓት ይዘረጋል፤
- በፖሊሲው የተካተቱ ወንጀሎችን በተመለከተ በአጥፊዎች ላይ የወንጀል ሙሉ ተጠያቂነት ለማረጋገጥ እንዲቻል ያለመከሰስ መብት ተፈፃሚነት እንዳይኖረው ይደረጋል፤
- በፖሊሲው እና በማስፈፀሚያ ሕጎች በግልጽ የሚቀመጡ ልዩ የምርመራ እና የክስ ሂደቶች እንደተጠበቁ ሆነው በሕገ-መንግስቱ፣ በወንጀል ሕጉ እና በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ላይ ከምርመራ እና ክስ ጋር በተያያዘ የተቀመጡ መርሆዎች እና ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ የምርመራ እና ክስ ሂደት ይተገበራል፤
- በአገር ውስጥ የማይገኙ ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ከሚገኙበት አገር ተላልፈው እንዲሰጡ ለማድረግ ተገቢ ስራ ይሰራል፤
- በየምርመራ ሂደት ሊደረስበት የማይችል ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ ያለው አጥፊ የሚገኝበትን ቦታ ለጠቆመ ወይም አጥፊው በጉልሕ የሰብአዊ መብት ጥሰት መሳተፉን የሚያሳይ ተጨባጭ ማስረጃ ላቀረበ ሰው የማበረታቻ ድጋፍ ወይም ሽልማት የሚሰጥበት ሥርዓት ይመቻቻል፤
- ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ምስክርነት የሚሰጡ ሰዎች በዚህ ምክንያት የበቀል እርምጃ እንዳይደርስባቸው አስፈላጊ ጥበቃ እና ድጋፍ የሚያገኙበት ሁሉን አቀፍ ሥርዓት ይዘረጋል።

### 2.1.3. የወንጀል ምርመራ እና ክስ የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት

የወንጀል ምርመራ እና የክስ ሂደቱ ህዝባዊ አመኔታ እንዲያገኝ እና አጠቃላይ የሽግግር ፍትሕ ሥርዓቱ በአገር-አቀፍ እና በዓለም-አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ የታለመውን የሽግግር ፍትሕ ዓላማ ለማሳካት ፍፁም መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም የወንጀል ምርመራ እና ክስ የሚከናወንባቸው ወንጀሎችን ግዝፈት እና ውስብስብነት፣ ሂደቱን ለመተግበር የሚያስፈልገውን ከፍተኛ ወጪ እና ሙያዊ አቅም፣ እንዲሁም አገራችን ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ የወንጀል ምርመራ እና ክስ ስራዎችን የሚመራ ተቋማዊ ሥርዓት መመስረት ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ አንፃር በሽግግር ፍትሕ ሂደት የሚከናወነው የወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ተግባር አሁን ካለው የወንጀል ምርመራ እና ዐቃቤ ሕግ ተቋም ውጪ በሆነ፣ ነጻ እና ገለልተኛ ሆኖ ራሱን ችሎ በሚቋቋም እና የሕዝብ አመኔታ በሚኖረው አዲስ የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋም አማካኝነት የሚከናወን ይሆናል። የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋሙ መርማሪዎችን እና ዐቃብያነ ሕግን የሚመራ ይሆናል።

የወንጀል ምርመራ እና የክስ ስራ የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓትን በተመለከተ የሚከተሉት ተጨማሪ የፖሊሲ አቅጣጫዎች እና ስልቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-

- የሚቋቋመውን የልዩ ዐቃቤ ህግ ተቋም አመራሮችን ምልመላ እና ሹመት ግልጽ፣ አካታችና አሳታፊ በሆነ፣ ብዝሀነትን ባማከለ አግባብ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ የሰብአዊና የዲሞክራሲ ተቋማት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን አካላት ባሳተፈ አግባብ የሚፈፀም ይሆናል፤
- የልዩ ዐቃቤ ህግ ተቋሙ የምርመራ ባለሙያዎች እና ዐቃብያነ ህግ ምልመላ እና ሹመት መልካም ስነ-ምግባርን፣ ልምድን እና ሙያዊ ብቃትን እና ሌሎች በህግ በግልጽ የሚቀመጡ መስፈርቶችን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲመረጡ ያደርጋል፤
- የምርመራ ባለሙያዎች እና ዐቃብያነ ህግ ምልመላ እና ሹመት ዖታን፣ ታማኝነትን፣ ገለልተኝነትን እና ብዝሃነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ይከናወናል፤
- አዲስ የሚቋቋመው የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋምን የህዝብ አመኔታ ለማሳደግ፣ እንዲሁም ጉልህ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን መርምሮ ክስ ከመምራት አንፃር ሊያጋጥም የሚችል የእውቀት እና የልምድ ክፍተትን ለመሙላት እንዲቻል ዓለም አቀፍ እውቀትና ልምድ ያላቸው የውጭ ባለሙያዎች በአማካሪነት እና በአሰልጣኝነት እንዲሳተፉ ይደረጋል፤
- በዚህ ስራ ላይ ለሚሰየሙ የምርመራ ባለሙያዎች እና ዐቃብያነ ህግ አስፈላጊ ህጋዊ ጥበቃ እና ከለላ የሚደረግበት ሥርዓት ይዘረጋል፤
- የልዩ ዐቃቤ ህግ ተቋሙ ነጻነቱን እና ገለልተኝነቱን በሚያረጋግጥ አግባብ በጀት ይመደብለታል፤ የተመደበውን በጀት የማስተዳደር ነጻነት እንዲኖረው ይደረጋል፤
- የተቋሙ የምርምራ ባለሙያዎች እና ዐቃብያነ ህግ ከኃላፊነት የሚነሱበት እና የሚተኩበት ሥርዓት የተቋሙን ነጻነት እና ገለልተኝነት በሚያረጋግጥ አግባብ እንዲዘረጋ ይደረጋል፤
- የልዩ ዐቃቤ ህግ ተቋሙ የምርመራ ባለሙያዎች እና ዐቃብያነ ህግን፣ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን የሚቀጥርበት እና የሚያስተዳድርበት ሥርዓት ይዘረጋል፤

– የሚቋቋመው የልዩ ዐቃቤ ህግ ተቋም በስራ ላይ ካሉ የፍትሕ ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፡፡

### 2.1.4. የፍርድ ሂደት የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት

በሽግግር ፍትህ ሂደት የወንጀል ተጠያቂነት ስራ የታለመውን ግብ እንዲያሳካ ለማድረግ በተለይም ኢትዮጵያ በተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች የተጣሉባትን ሰብዓዊ መብቶችን የመጠበቅ እና ተጠያቂነትን የማረጋገጥ ግዴታዋን በተገቢ መልኩ እንድትወጣ ለማስቻል ነጻ እና ገለልተኛ የዳኝነት ተቋም ማደራጀት የሽግግር ፍትሕ ልዩ ባሕሪ የሚፈለገው መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም በሚተገበረው የሽግግር ፍትህ ስርዓት በተለይም የወንጀል ተጠያቂነትን በመመስረት ሂደት አገራዊ ፍርድ ቤቶች ያላቸውን ቅድሚያ የመዳኘት ስልጣንን መሰረት በማድረግ በማህበረሰቡ፣ በተጎጂዎች እና በተከሳሶች ዘንድ አመኔታ እና ተቀባይነት የሚኖረው፣ አቅም እና ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችን ያካተተ ፣ የተጎጂዎችን ተሳትፎ የሚያረጋግጥ፣ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ስር የተለየ የራሱ አደረጃጀት የሚኖረው ልዩ ችሎት የሚደራጅ ይሆናል፡፡ ልዩ ችሎቱ ነጻ እና ገለልተኛነቱን ሊያረጋግጥ በሚችል አግባብ ይደራጃል።

የፍርድ ሂደት የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓትን በተመለከተ የሚከተሉት ተጨማሪ የፖሊሲ አቅጣጫዎች እና ስልቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-

– ልዩ ችሎቱ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስር ይቋቋማል፡፡ የይግባኝና የሰበር የዳኝነት ስልጣንን በተመለከተ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር ተመሳሳይ ልዩ የይግባኝና የሰበር ሰሚ ችሎት ይደራጃል፡፡
– የልዩ ችሎቱ ሃላፊነቱን የመወጣት አቅሙን ከፍ ለማድረግ፣ አግባብነት ያላቸውን አለም አቀፍ መስፈርቶች የጠበቀ አሰራር ለመከተል እንዲያግዘው የውጭ ሀገራት ባለሙያዎች በአማካሪነት እና አሰልጣኝነት እንዲሳተፉ ይደረጋል፤
– በልዩ ችሎቱ የሚመደቡ ዳኞች በሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ያልተሳተፉ ወይም በመብት ጥሰት የማይጠረጠሩ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የልየታ እና የማጥራት ስራ የሚካሄድበት ልዩ ሥርዓት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይዘረጋል፤
– በልዩ ችሎቱ የሚመደቡ ዳኞች ሁሉ በወንጀል ህግ፣ በዓለም አቀፍ የወንጀል ህግ፣ በዓለም-አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ወይም በዓለም-አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ጉዳዮች ከፍተኛ ልምድ፣ የላቀ ብቃት እና እውቀት ያላቸው እንዲሆኑ ይደረጋል፤
– የዳኞች ምደባ ከመልካም ስነ-ምግባር፣ ልምድ እና ሙያዊ ብቃት፣ እንዲሁም በህግ በግልጽ በሚቀመጡ ሌሎች መስፈርቶች መሰረት ይካሄዳል፤
– የዳኞች ምደባ ዖታን፣ አመኔታን፣ ገለልተኝነትን እና ብዝሃነትን በሚያረጋግጥ አግባብ ይከናወናል፤
– በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስር የሚደራጀው የልዩ ችሎቱ ሥልጣን በማናቸውም ሁኔታ በውክልና ሊሰጥ አይችልም፤ ሆኖም፣ እንደ አስፈላጊነቱ ለፌዴራል ጠቀላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ የሆኑ ልዩ ችሎቶች በክልል ደረጃ ሊያቋቁሙ ይችላሉ
– ልዩ ችሎቱ በስሩ የሚወድቁ ጉዳዮችን በተመለከት ቅድሚያ የዳኝነት ስልጣን እንዲኖረው ይደረጋል፤
– ልዩ ችሎቱ በስሩ ሙያዊ ብቃት እና ልምድ ያላቸው ሬጅስትራር እና የተከላካይ ጠበቃ አደረጃጀት፣ የተጎጂዎች ተሳትፎ ማስተባበሪያ፣ የአማካሪ ባለሙያዎች እና ሌሎች ደጋፊ የስራ ሂደቶች እንዲኖሩት ይደረጋል፤
– ልዩ ችሎቱ የዳኝነት ስራውን የአገር ውስጥ ህጎችን እና ዓለም-አቀፍ ህግ እና መርህን በመከተል የሚሰራ ይሆናል፤
– የልዩ ችሎቱን፣ የዳኞችን ነጻነት እና ገለልተኝነት የሚያረጋግጡ ህጎች እንዲወጡና የአሰራር ስርዓቶች እንዲዘረጉ ይደረጋል፤
– ዳኞች የሚነሱበት እና የሚተኩበት ሂደት የልዩ ችሎቱን ነጻነት እና ገለልተኝነት በሚያረጋግጥ አግባብ እንዲሆን አስፈላጊ የህግ እና የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤



Office of the Prime Minister

- ለፍርድ ቤት የሚመደበው በጀት እና የበጀት አስተዳደር የልዩ ችሎቱን ነጻነት እና ገለልተኝነት በሚያረጋግጥ አግባብ እንዲሆን አስፈላጊ የአሰራርና አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል።

## 2.2. እውነትን ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና የዕርቅ ተግባር

እውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና የዕርቅ ተግባራት በተለያዩ ዘመናት የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን እና በደሎችን መሰረታዊ ምክንያት በተሟላ መልኩ በመለየት የተጎጂዎችን እውነቱን የማወቅ መብት ለማረጋገጥ ያስችላሉ፡፡ አልፎም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት፣ ጦርነት፣ ግጭት ወይም ጭቆና ባስከተለው መጎዳዳት፣ ጥላቻ እና መፈራራት ምክንያት ተለያይተው የነበሩ ሰዎች እና የሕብረተሰብ ክፍሎች ግንኙነታቸውን እንደገና ለመገንባት፣ ቁስላቸውን ለመፈወስ፣ በደሎች እንዳይደገሙ ለማድረግ እና ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን ጉልህ ፋይዳ አለው።

ስለሆነም እውነት የማፈላለግ፣ ይፋ የማውጣት እና የዕርቅ ተግባርን የሚመለከተው የሽግግር ፍትሕ ስልት በአገራችን በሚተገበረው የሽግግር ፍትሕ ሂደት ነባራዊ ሁኔታዎችን ባገናዘበ እና ከሌሎች የሽግግር ፍትሕ ስልቶች ጋር በተናበበ መልኩ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል።

### 2.2.1. እውነትን ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና ዕርቅ ተግባራዊ የሚደረግባቸው ጉዳዮች

እውነት የማፈላለግ እና ይፋ የማውጣት ስራ ተግባራዊ የሚደረግባቸው ጉዳዮችን በአግባቡ መለየት እና መወሰን ሂደቱ የታለመለትን ዓላማ እንዲያሳካ ለማድረግ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። በሽግግር ፍትሕ ስርዓቱ ማእቀፍ የሚተገበር እውነት የማፈላለግ፣ ይፋ የማውጣት እና የዕርቅ ስራ 'በሁሉም ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች' ላይ በማተኮር የጥሰቶችን መሠረታዊ ምክንያቶች፣ ተከታታይነት፣ ስልታዊነት፣ መጠነ-ሰፊነት፣ ዓይነት እና የጉዳት መጠን በመለየት ተግባራዊ ይደረጋል።

በመሆኑም ሌሎች 'ጉልህ ያልሆኑ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች' በባህላዊ እና ክልል–አቀፍ የግጭት አፈታት እና ዕርቅ ሥርዓቶች የሥረ-ነገር ስልጣን ማእቀፍ ስር የሚያርፉ እና መፍትሔ የሚያገኙ ይሆናል፡፡

እውነትን የማፈላለግ፣ ይፋ የማውጣት እና የዕርቅ ስራዎች የሚፈፀሙባቸው ጉዳዮችን በተመለከተ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-

- እውነት የማፈላለግ፣ ይፋ የማውጣት እና የዕርቅ ስራዎች ስረ–ነገር 'በሁሉም ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች' ላይ የሚወድቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሂደቱ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው ጥሰቶች ግን በመብት ጥሰቶቹ ክብደት እና ጉልህነት ላይ ብቻ ተመስርቶ የሚወሰን አይሆንም፤ ስለሆነም የጥሰቶቹን ተከታታይነት፣ ስልታዊነት ወይም መጠነ-ሰፊነት ግምት ውስጥ በማስገባት መሰል ጥሰቶች የእውነት ማፈላለግ ተግባር አካል እንዲሆኑ ይደረጋል፤
- በአገራችን በተለያዩ ጊዜያት ለግጭቶች መንስኤ የሆኑ የታሪክ አረዳዶች እና ትርክቶች የተከሰቱበት የጊዜ ማእቀፍ ወሰን ሳይደረግበት ሁሉንም በመመርመር፣ ትርክቱን በማጥራት እና በመለየት እውነትን ይፋ የማውጣት እና እውቅና የመስጠት ተግባር ይከናወናል፤
- እውነትን በማፈላለግ ሂደት ስልጣን በሚኖረው የሀቅ አፈላላጊ ኮሚሽን ፊት በፈቃዳቸው በመቅረብ እውነትን የሚያወጡ ወይም ቃል የሚሰጡ አጥፊዎች የሰጡት ማናቸውም ቃል በፍርድ ሂደት እንደ ማስረጃ ጥቅም ላይ እንዳይውልባቸው ጥበቃ (use immunity) ይደረግላቸዋል፤ ዝርዝሩ በሕግ የሚወሰን ይሆናል፤

- ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ጉዳታቸውን በዝርዝር እንዲያስረዱ በማድረግ እውነትን በማጥራት ሂደት ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይደረጋል፤
- የእውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና የዕርቅ ተግባራት ለጾታዊ ጥሰቶች፣ ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ልዩ በደሎች እና ለሌሎች ልዩ ትኩረት የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎች ጉዳዮች ተገቢ ትኩረት በሚሰጥ አግባብ ይከናወናሉ፤
- በእውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና የዕርቅ ተግባራት ማእቀፍ ያለፉ ጊዜያት ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ዝርዝር መረጃዎች በአግባቡ በመሰነድ ጥፋቶች እንዲታወቁ እና ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ የሚያግዙ የሰነዳ ስራዎች ይሰራሉ፤ የተጣራው እውነት ለማህበረሰብ የማሳወቅ፣ እንዲሁም ለተጎጂዎች ሰቆቃ ሕዝባዊ እውቅና የመስጠት ስራዎችን የሚመሩ አሰራሮች ይዘረጋሉ፡፡

### 2.2.2. እውነትን የማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና የዕርቅ ተግባር የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት

በሽግግር ፍትሕ ሥርዓት ማዕቀፍ የእውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና የዕርቅ ተግባራት ነጻነትን፣ ገለልተኛነትን፣ ተቀባይነትን እና ተአማኒነትን በሚያረጋግጥ እና ብቃት በተላበሰ መንገድ የሚተገበሩበት ተቋማዊ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው።

በመሆኑም እውነትን የማፈላለግ፣ ይፋ የማውጣት እና የዕርቅ ተግባራት ከተጽዕኖ እና ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት ነጻ እና ገለልተኛ ሆኖ በሚቋቋም አዲስ የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት እንዲከናወኑ ይደረጋል።

እውነትን የማፈላለግ፣ ይፋ የማውጣት እና የዕርቅ ተግባራት የሚከናወኑበት ተቋማዊ ሥርዓትን በተመለከተ የሚከተሉት አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-

- የሚቋቋመው ኮሚሽን ምህረት የመስጠት ሥራን የሚመለከት ተደራቢ ኃላፊነት ይኖረዋል፤ በተጨማሪም ኮሚሽኑ የማካካሻ ስራዎችን የሚመራ መዋቅር በሥሩ ያደራጃል፤
- ኮሚሽኑ የጾታ፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ የሲቪክ ማህበረሰብ አባላት እና ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ውክልና ያለው ሆኖ ብቁ እና ገለልተኛ ባለሙያዎችን የሚያካትት አደረጃጀት እንዲኖረው ይደረጋል፤
- ለኮሚሽነርነት የሚያበቁ ዝርዝር ጉዳዮች በሕግ ይደነገጋሉ፤ ሆኖም የኮሚሽኑ ኮሚሽነሮች ምርጫ የሕዝብ እና የባለድርሻ አካላትን አስተያየት እና ተሳትፎ ግምት ውስጥ በሚያስገባ አግባብ ይከናወናል። የኮሚሽነሮች ምልመላ እና ሹመት ግልጽ፣ አካታችና አሳታፊነ በሆነ፣ ብዝሀነትን ባማከለ አግባብ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች፣ የመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ የሰብአዊና የዲሞክራሲ ተቋማት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን አካላት ባሳተፈ አግባብ የሚፈፀም ይሆናል፤
- የኮሚሽነሮች መረጣ እና ሹመት የፆታ፣ እውቀት፣ የስነ ምግባር፣ ሙያዊ ታማኝነት፣ ገለልተኝነት እና የብዝሃነት መገለጫዎችን ታሳቢ ያደረገ ይሆናል፤
- የኮሚሽኑን ተቋማዊ ብቃት ለማጎልበት እና ልምድ ለመቅሰም፣ እንዲሁም ከተአማኒነት ጋር የሚያያዙ ጥያቄዎችን ለመመለስ እንዲቻል ከተለያዩ ሀገራት የተወጣጡ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች በኮሚሽኑ ተቋማዊ አደረጃጀት ውስጥ በአማካሪነት እና ድጋፍ ሰጪነት እንዲካተቱ ይደረጋል፤
- በትግበራ ምእራፍ የኮሚሽኑን ነጻነት እና ገለልተኝነት የሚያረጋግጡ አሠራሮች ይዘረጋሉ፤
- ኮሚሽኑ ባለሙያዎች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን የሚቀጥርበት እና የሚያስተዳድርበት ሥርዓት ይዘረጋል፤

– የኮሚሽኑን ተቋማዊ ነጻነት እና ገለልተኝነት በሚያረጋግጥ መጠን በጀት እና በጀቱን የሚያስተዳድርበት ሥርዓት ይዘረጋል።

## 2.3. በቅድመ–ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረት

የሽግግር ፍትሕ ሂደቱ በተለያዩ ጊዜያት የተፈጸሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና በደሎችን የሚዳስስ እንደመሆኑ መጠን የተጎጂዎች ይሁን የአጥፊዎች ቁጥር እጅግ ከፍተኛ እንደሚሆን ይጠበቃል። በዚህ ረገድ ሁሉንም ወንጀሎች/ጥሰቶች በክስ ሂደት እንዲያልፉ ማድረግ አይቻልም። ሁሉም ጥፋቶች በወንጀል ተጠያቂነት ማዕቀፍ እንዲወድቁ ይደረግ ቢባል የእውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና የዕርቅ ተግባራትን ተፈፃሚ ማድረግ የሚቻልበትን እድል ያስቀራል። በሌላ በኩል ለተፈጸሙ ጥሰቶች ሁሉ ምህረት የሚሰጥበትን ሁኔታ መደንገግ የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስቀር እና ዓለም አቀፍ ግዴታን የሚቃረን ከመሆኑም በላይ የተሟላ የሽግግር ፍትሕ ተግባራዊ ለማድረግ ተግዳሮት ይፈጥራል።

ስለሆነም በቅድመ–ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረትን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል። ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያ ተግባራዊ በሚደረገው የሽግግር ፍትሕ ሂደት በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረት ተግባራዊ ይደረጋል።

### 2.3.1. ምህረት የማይሰጥባቸው ሁኔታዎች

አገራችን የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶችና የሰብአዊነት ሕጎች ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የፈፀሙ አጥፊዎች ከተጠያቂነት ማምለጥ እንደማይኖርባቸው ደንግገዋል። እነዚህ ሰነዶችን መሰረት በማድረግም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ–መንግስት በአንቀጽ 28(1) ላይ በምህረት ሊታለፉ የማይችሉ ወንጀሎችን ዘርዝሮ አስቀምጧል።

በመሆኑም በዚህ ፖሊሲ 'ለወንጀል ተጠያቂነት' ዓላማ 'ጉልህ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች' እና 'ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎችን' በተመለከተ በተሰጠው ትርጉም መሰረት 'በጉልህ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች' የምህረት ተጠቃሚ አይሆኑም።

### 2.3.2. ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ ቅድመ ሁኔታዎች

የሕግ የበላይነት እና ተጠያቂነትን በማያስቀር መልኩ በቅድመ–ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ ምህረት የሽግግር ፍትሕ ሂደትን በማሳለጥ ረገድ የጎላ ሚና ይኖረዋል። ስለሆነም ምህረትን በመስጠት ሂደት የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች እና ስልቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ:-

– እንደአግባብነቱ በህግ የሚወሰኑ ሌሎች ቅድመ–ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ማመልከቻ በማቅረብ የምህረት ተጠቃሚ ለመሆን የሚከተሉት ቅድመ-ሁኔታዎች ተፈፃሚ ይደረጋሉ:- በጉልህ ወንጀሎች/ጥሰቶች ላይ ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያለው አለመሆን፣ እውነት በማውጣት እና በምርመራ ሂደት መተባበር፣ ጥፋትን ማመን እና መጸጸት፣ በይፋ ህዝብን እና ተጎጂዎችን ይቅርታ መጠየቅ፣ እንዳስፈላጊነቱ እና እንደ ሁኔታው ለተፈጸመው በደል በማካካሻ ሂደት ለመሳተፍ ፈቃደኛ መሆን፣ በበጎ ፈቃድ ሰራ ላይ በመሳተፍ ህዝባዊ አገልግሎት ለመስጠት መስማማት፣ ወንጀሉ የተፈፀመበትን ምክንያት (motive) በማየት እንዳስፈላጊነቱ ከህዝባዊ ሀላፊነት ለመልቀቅ ፈቃደኛ መሆን፣ ተመሳሳይ የወንጀል ሪከርድ አለመኖር፣ እና ተመሳሳይ ጥሰቶች እንደማይፈጽም ቃል መግባት፣

- በቅድመ-ሁኔታ የሚሰጥ ምህረት የተፈለገውን ዓላማ እንዲያሳካ እና የምህረት ተጠቃሚው ወደ ህብረተሰቡ ሲቀላቀል በቀል እና ቁርሾ እንዳይፈጠር ለመከላከል ሂደቱ ተጎጂን ማዕከል እንዲያደርግ እና በፖሊሲው የተገለጹ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች ሚና ከግምት እንዲያስገባ ይደረጋል፤
- የምህረት አሰጣጥ ሂደቱ ግልጽ፣ ገለልተኛ እና ተአማኒነት በሚኖረው አግባብ ይከናወናል፤
- ምህረት ከተሰጠ በኋላ ተጠቃሚዎች ወደ ሕብረተሰቡ የሚቀላቀሉበትን ሥርዓት፣ እንዲሁም ምህረት ከተሰጠ በኋላ የሚነሳበት አግባብ በህግ እንዲወሰን ይደረጋል፡፡

የምህረት ተጠቃሚ ለመሆን አመልክቶ ከላይ የተገለጹትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ ያልተገኘ አመልካች ጉዳዩ በመደበኛ የወንጀል ፍትሕ ሥርዐት የሚታይበት አሰራር እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡

### 2.3.3. የምህረት ተግባር የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት

ምህረትን ከእውነት ማፈላለግ፣ ማውጣትና ከዕርቅ ተግባራት ጋር በተሰናሰለ እና ተመጋጋቢ በሆነ መንገድ መተግበር አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ እንዲቻል የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽኑ – ምህረት የመስጠቱን ተግባር በተደራቢነት እንዲያከናውን ይደረጋል፡፡

የምህረት አሰጣጥ ስራ የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓትን በተመለከተ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎችና ስልቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡-

- የምህረት ስራዎችን የሚያከናውን ገለልተኛ የሆነ፣ በዘርፉ የዳበረ እውቀት እና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን በአማካሪነት የያዘ መዋቅር በኮሚሽኑ ስር ይደራጃል፤
- የምህረትን ጉዳይ በሚመለከት የሚዋቀረው አደረጃጀት የምህረት ጥያቄን ከመቀበል አንስቶ በቀረቡ አቤቱታዎች ላይ ለኮሚሽኑ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብበት ስርዐት በህግ ይዘረጋል፤
- በምህረት አሰጣጥ ሂደት የተጎጂን እና ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማትን ተሳትፎ እንዲሁም የምህረት አሰጣጥ ስነ ሥርዓትን የሚደነግግ ሕግ ይወጣል፡፡

## 2.4. ማካካሻ

በሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና ኢ-ፍትሀዊ አሰራሮች ምክንያት ተጎጂ የሆኑ ግለሰቦች እና ማህበረሰቦች የጉዳቶችን ዓይነት እና መጠን መሰረት በማድረግ በሚዘረጋ ሁሉን–አቀፍ የማካካሻ ስርአት እንዲያልፉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የሽግግር ፍትሕ ሂደት እንደ መልሶ ማቋቋም፣ ማገገሚያ፣ እርካታ፣ የመታሰቢያ እና ማስታወሻ ክንዋኔ፣ በይፋ ይቅርታ መጠየቅ እና ሌሎች ተያያዥ የማካካሻ ዓይነቶችን ተግባራዊ የሚያደርግ ስርአት ተፈፃሚ ያደርጋል።

### 2.4.1. ተግባራዊ የሚደረጉ የማካካሻ ዓይነቶች እና ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች

በሽግግር ፍትሕ ሂደት የሚከተሉት የማካካሻ አይነቶች አቅምን እና ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-

- መልሶ ማቋቋም፣ የማገገሚያ እርምጃዎች፣ ፈውስ፣ የመታሰቢያ እና ማስታወሻ ክንዋኔዎች፣ የጥሰቶችን ሙሉ ሀቅ ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና እውቅና መስጠት፤
- ለተፈጸሙት በደሎች በመንግስት ደረጃ ይፋዊ ይቅርታ መጠየቅ፤
- የተጎጂዎችን አንገብጋቢ ወይም አስቸኳይ ችግሮች በተወሰነ መልኩ ለመቅረፍ ይረዳ ዘንድ፣ እንዲሁም ልዩ ትኩረት የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎችን ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት ዘላቂ የማካካሻ ሥርዓት ተግባራዊ እስኪደረግ ድረስ መልሶ ማቋቋም፣ የማገገሚያ እርምጃዎች እና ሌሎች አስፈላጊ የማካካሻ ዓይነቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፤
- የማካካሻ አይነቶች ተግባራዊ ሲደረጉ አይነታቸውን፣ ባህሪያቸውን እና የአፈጻጸም ሂደቶቹን መሰረት በማድረግ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ሚና እንዲኖራቸው ይደረጋል፤
- የማካካሻ ሥርዓት አተገባበር ልዩ ትኩረት የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎችን በተለይም የሕጻናት፣ የሴቶች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያንን ፍላጎት ባገናዘበ መንገድ ይፈፀማል።

### 2.4.2. ማካካሻ የሚመራበት ተቋማዊ ሥርዓት

የማካካሻ ስራን ምህረት ከመስጠት እና ከእውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣትና ዕርቅ ተግባር ጋር በተሰናሰለ መንገድ መተግበር አስፈላጊ በመሆኑ – የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽኑ የማካካሻ ስራዎችን የሚያከናውን ይሆናል፡፡

በዚህ ረገድ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይሆናሉ፡-

- የማካካሻ አይነቶች ተግባራዊ ከመደረጋቸው በፊት አሰራሮችን እና ታሳቢ የሚደረጉ ሁኔታዎችን የሚዘረዝር በጥናት ላይ የተመሰረተ የማካካሻ ህግ ማዕቀፍ እና መርሀ-ግብር እንዲዘጋጅ ይደረጋል፤
- አንገብጋቢ ወይም አስቸኳይ ችግሮችን በተወሰነ መልኩ ለመቅረፍ ይረዳ ዘንድ ዘላቂ የማካካሻ ሥርዓት ተግባራዊ እስኪደረግ ድረስ ኮሚሽኑ ጣልቃ-ገብ የማካካሻ ተግባራትን ያከናውናል፤
- ተጎጂዎችን የማቋቋም/የመደገፍ ሥራዎችን ለመምራት የማቋቋሚያ እና ድጋፍ ፈንድ በህግ ይቋቋማል፤
- ገለልተኛ የሆነ፣ የኮሚሽኑን የማካካሻ ስራዎች የሚያሳልጥ እና በዘርፉ የዳበረ እውቀት እና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን በአማካሪነት የያዘ መዋቅር በኮሚሽኑ ስር ይደራጃል፤
- በኮሚሽኑ ስር የሚዋቀረው አደረጃጀት የማካካሻ ማዕቀፍ እና መርሀ-ግብር ይነድፋል፤ በአቤቱታዎች እና ውሳኔ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ለኮሚሽኑ የውሳኔ ሀሳብ የሚቀርብበት ስርአት ይዘረጋል፤ ለማካካሻ የሚውል የበጀት ምንጭ ለይቶ ያቀርባል።

## 2.5. ተቋማዊ ማሻሻያ

በግጭቶች እና በተፈፀሙ ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አስተዋጽኦ ወይም ተሳትፎ የነበራቸውን ተቋማት እና ግለሰቦችን ባሉበት ማስቀጠል ለሚታሰበው የሽግግር ሂደት እንቅፋት ይፈጥራል፡፡ በተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች አስተዋጽኦ በነበራቸው ወይም ኃላፊነታቸውን ባለመወጣት ጉዳት እንዲደርስ ባደረጉ ተቋማት፣ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ላይ አስፈላጊውን የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ ጥሰቶቹ እንዳይደገሙ፣ ተቋማቱም የሕዝብ አመኔታ የተቸራቸው፣ መሰረታዊ መብቶችንና ነጻነቶችን የማክበር እና የማስከበር ቁመና እንዲኖራቸው ለማድረግ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

ስለሆነም በሚተገበረው የሽግግር ፍትሕ ሂደት ሰፊ የተቋማዊ ማሻሻያ ስራ ተግባራዊ ይደረጋል። ከዚህ አኳያ ተቋማዊ መሻሻያን በተመለከተ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-

- የማሻሻያ ስራ ተግባራዊ የሚደረግባቸው ተቋማት፣ ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎች፣ በተፈፀሙ ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች የነበራቸው ድርሻ እና ሚና፣ እንዲሁም ለተፈፀሙ ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች መነሻ የሆኑ ወይም አስቻይ ሁኔታዎችን የፈጠሩ የፖሊሲ፣ የህግ እና የአሰራር ማዕቀፎችን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት መርሆዎችን ባከበረ እና ከዓለም አቀፍ አሰራር ጋር በተጣጣመ መልኩ ይለያሉ፤
- የተቋማት ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በመሳተፍ ወይም ኃላፊነትን ባለመወጣት በተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች ላይ እንደነበራቸው የተሳትፎ መጠን ወይም የሥነ-ምግባር/ሙያዊ ብቃት ማነስ ሁኔታ እየታየ ከስራ እንዲነሱ፣ በአስተዳደራዊ እርምጃ ወይም በወንጀል ተጠያቂ እንዲሆኑ ወይም ሌሎች አስፈላጊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ይደረጋል፤
- የተለዩ እና ለጥሰት መነሻ የሆኑ ምንጮችን እና ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ተቋማትን ለማሻሻል እና ለመለወጥ የሚያስችሉ የአጭር እና የረጅም ጊዜ ፕሮግራሞች ተነድፈው ተግባራዊ ይደረጋሉ፤
- ተቋማት፣ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች በህግ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ተቋማዊ እና ሙያዊ ነጻነት እና ገለልተኝነት ባስጠበቀ አግባብ እንዲሰሩ ለማድረግ የሚያስችል እንደ አስፈላጊነቱ የተቋማት ስልጣን፣ አደረጃጀት እና ተጠሪነትን የሚመለከቱ የህግ፣ የፖሊሲ ወይም አሰራር ማሻሻያዎች ይደረጋሉ፤
- የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንዳይደገሙ እና ለሰብአዊ መብቶች መከበር፣ ለመልካም አስተዳደር መስፈን እና የህግ የበላይነት መረጋገጥ አስቻይ ሁኔታ የሚፈጥሩ የህግ እና የፖሊሲ ማዕቀፎች በጥናት ላይ ተመስርተው እንዲወጡ ይደረጋል፤
- የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ የሚያስችል፣ ለመብት ጥሰት ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ትኩረት የሚሰጥ እና ህብረተሰቡን ማዕከል የሚያደርግ የተቋማት የወንጀል መከላከል አቅም ማጠናከሪያ ስልት በጥናት ላይ ተመስርቶ ይተገበራል፤
- ለተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች የተጋለጡ ተጎጂዎች እና ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጥቅም ከማስጠበቅ አኳያ የተቋማት ማሻሻያ እርምጃዎች ተለይተው ተግባራዊ ይደረጋሉ፤
- የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ እንዲቻል በፌዴራል ተቋማት እንዲሁም በፌዴራል እና በክልል ተቋማት መካከል ያለው ቅንጅታዊ አሰራር፣ ድጋፍ እና ክትትል ሥርዓት እንዲጠናከር ይደረጋል፤
- የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንዳይደገሙ ከማድረግ እና የሰብአዊ መብቶች መከበር ባህል እንዲዳብር የተቋማት፣ የባለሙያዎች እና ሰራተኞች አቅም ግንባታ እና የመፈፀም አቅም ለማሳደግ የሚያስችል ስራ ከአጋር አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት አሰራር ይዘረጋል፤

የልየታ፣ የማጥራት እና የማሻሻያ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችል ሁሉን አቀፍ ህግ እንዲወጣ ይደረጋል።

### 2.5.1. የተቋማዊ ማሻሻያ ስራ ትኩረት የሚያደርግባቸው ተቋማት

ከመብቶች ጥበቃ እና አፈፃፀም ጋር የተያያዘ ሀላፊነት ያላቸው ሁሉም ተቋማት ለሰው ልጅ በተፈጥሮ የተቸሩ መብቶች እና ነጻነቶችን የማክበር እና የማስከበር ግዴታቸውን መወጣት እንዲችሉ እና የተቋቋሙለትን ዓላማ እንዲያሳኩ ለማድረግ በትኩረት

መስራት መሰረታዊ ሁኔታ ነው። ይሁን እንጂ ካለው ውስን አገራዊ አቅም እና የሽግግር ፍትሕ ሂደት ባህሪ አንጻር ሁሉንም ተቋማት በማሻሻያ ሥርዓት ሂደት እንዲያልፉ ማድረግ አይቻልም።

ስለሆነም በሽግግር ፍትሕ ሂደት ማዕቀፍ የማሻሻያ ስራዎች ትግበራ ትኩረት ውስን ይሆናል። በዋናነትም በሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ በተሳተፉ ሰዎች፣ የዜጎችን ሰብአዊ መብት በማክበር ወይም በማስከበር ረገድ ኃላፊነታቸውን ባልተወጡ እና ያለፉ ጥፋቶች እንዳይደገሙ በማድረግ ረገድ ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ በሚችሉ አገራዊ እና ክልላዊ የፍትሕ፣ የፀጥታ እና የደህንነት ተቋማት፣ የሚዲያ ተቋማት፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ሰብአዊ መብትን ከማስከበር አኳያ ኃላፊነታቸውን ባልተወጡ ተቋማት፣ እና ለሰብአዊ መብት ጥሰት አስቻይ ሁኔታን በፈጠሩ ህጎች፣ ፖሊሲዎች እና አሰራሮች ላይ ቅድሚያ በመስጠት የማሻሻያ ስራ የሚተገበር ይሆናል።

### 2.5.2. የተቋማዊ ማሻሻያ ስራ የሚመራበት ተቋማዊ ሥርዓት

የተቋማዊ ማሻሻያ ስራው ውጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተቀባይነት እና የህዝብ አመኔታ እንዲኖረው ለማድረግ ነጻ፣ ገለልተኛ እና ብቃት ባለው ተቋም አማካኝነት እንዲመራ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ስለሆነም ስራውን የሚመራ ነጻ፣ ገለልተኛ እና የህዝብ አመኔታ ያለው ኮሚሽን በህግ እንዲቋቋም ይደረጋል።

በተጨማሪም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-

- ኮሚሽኑ ሙያዊ ብቃት፣ ልምድ እና መልካም ስነ-ምግባር ባላቸው ነጻ እና ከፖለቲካ ገለልተኛ በሆኑ ኮሚሽነሮች እንዲመራ ይደረጋል፤ ሙያዊ ብቃት እና ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች ይደራጃል፤
- ኮሚሽኑ ተቋማትን የመለየት እና የማጥራት ስራ በማከናወን እና የማሻሻያ እርምጃዎችን በመለየት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ለማስወሰን የሚያስችል ስልጣንና ተግባር እንዲኖረው ይደረጋል፤
- በሚመረጡ ተቋማት ላይ የመለየት እና የማጥራት ሂደቱ የሚመራበት ዝርዝር ሥርዓት ይዘረጋል፤
- ከዳኝነት አካላት ጋር በተገናኘ ኮሚሽኑ የዳኞችን ልየታ እና ማጥራት ስራ የሚያከናውን ራሱን የቻለ አደረጃጀት ይኖረዋል፤ የዳኞች ልየታ እና ማጥራት ስራው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ–መንግስት ላይ ከተቀመጡ ጥበቃዎች እና ከሚጠበቁ አሰራሮች ጋር በሚጣጣም አግባብ በኮሚሽኑ ይከናወናል፤
- ኮሚሽኑ የመለየትና የማጥራት ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት የተቋማቱን መሰረታዊ ችግር በአግባቡ ለመረዳት እንዲችል በተቋማቱ የሚገኙ እውቀት ያላቸው ባለሙያዎች እንዲሳተፉ ይደረጋል፤
- የኮሚሽኑ የመለየት፣ የማጥራት እና የማሻሻያ ስራ ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶችን ባከበረ፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን በተከተለ እና የሽግግር ፍትሕ ተቋማዊ ማሻሻያ ዓላማዎችን ሊያሳካ በሚያስችል አግባብ ለማከናወን እንዲቻል ኮሚሽኑ በዘርፉ ልምድ እና እውቀት ያላቸው አማካሪዎች እንዲኖሩት ይደረጋል፤
- የኮሚሽነሮች ምልመላ እና ሹመት ግልጽ፣ አካታችና አሳታፊነ በሆነ፣ ብዝሀነት ባመከለ አግባብ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች፣ የመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ የሰብአዊና የዲሞክራቲክ ተቋማት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን አካላትን ባሳተፈ አግባብ የሚፈፀም ይሆናል፤
- ኮሚሽኑ ባለሙያዎች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን የሚቀጥርበት እና የሚያስተዳድርበት ሥርዓት ይዘረጋል፤

- ክልሎች የተቋማዊ ማሻሻያ ስራዎችን የሚሰራ ተቋም በህግ ያቋቁማሉ፤ ክልላዊ ተቋማቱ ከዚህ ፖሊሲ እና ዓለምአቀፍ የሰብአዊ መብት መርሆዎች ጋር በሚጣጣም አግባብ የሚመሰረቱ ይሆናል፤
- ኮሚሽኑ በክልል ደረጃ በሚቋቋሙ ተቋማት የሚሰሩ የልየታ፣ የማጥራት እና የማሻሻያ ስራዎችን በቅርበት የመደገፍ እና የማስተባበር ሚና እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

## 2.6. የሽግግር ፍትሕ ተግባራዊ የሚደረግበት የጊዜ ወሰን

የሽግግር ፍትሕ ሥርዓት ትግበራ ግልፅ የጊዜ ወሰን ሊኖረው ይገባል። ለዚህ ዓላማ የሚቀመጥ የጊዜ ወሰን በተቻለ መጠን ሁሉ የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን፣ የተዛነፉ የታሪክ አረዳዶች፣ ልዩነቶች እና ቁርሾዎች እና የተከሰቱ በደሎችን የሚያካትት እና ለዘላቂ ሽግግር መንገድ የሚከፍት መሆን አለበት፡፡

ስለሆነም የሽግግር ፍትሕ የጊዜ ወሰን ለወንጀል ተጠያቂነት ዓላማ 'የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ–መንግስት ከፀደቀበት ከ1987 ጀምሮ' ያለው የጊዜ ወሰን ተፈፃሚ ይደረጋል፡፡ በሌላ በኩል 'ለእውነት ማፈላለግ፣ ዕርቅ ማስፈን እና ማካካሻ ስራዎች ዓላማ' ጥሰቶች እና ቅራኔዎችን ከመሰረታቸው በማጥራት ለመመርመር፣ ስብራቶች እንዲሽሩ እና እንዲጠገኑ ለማድረግ እና ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት እንዲቻል የሽግግር ፍትሕ ሂደቱ የተፈፃሚነት ወሰን 'መረጃ እና ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ ድረስ' ይሆናል።

## 2.7. በሽግግር ፍትሕ ትግበራ የክልሎች ሚና

በሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደት ክልሎች የሚኖራቸውን ሚና ለይቶ እና ዘርዝሮ ማስቀመጥ በፌዴራል እና ክልሎች መካከል መልካም የስራ ግንኙነት በመፍጠር የሽግግር ፍትሕ ዓላማዎችን በተሻለ ደረጃ ለማሳካት ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ ስለሆነም በአገር አቀፍ ደረጃ በሚተገበረው የሽግግር ፍትሕ ሥርዓት ማዕቀፍ ክልሎች ጉልህ ሚና እንዲኖራቸው ይደረጋል።

በዚህ ረገድ ክልሎች በሁለት መንገዶች የሚገለፁ ሚናዎች ይኖሯቸዋል፡፡ የመጀመሪያው በአገር–አቀፍ ተቋማት የሚከናወኑ ስራዎችን በማገዝ ላይ የሚያተኩር ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በዚህ ፖሊሲ አጠቃላይ እሳቤዎች፣እሴቶች እና መርሆዎች ላይ በመመስረት ውስን የሽግግር ፍትሕ ስራዎችን ራሳቸው በባለቤትነት የሚመሩበትን ሂደት የሚመለከት ነው፡፡

ከዚህ አንፃር በአገር–አቀፍ ተቋማት የሚከናወኑ ስራዎችን በማገዝ ረገድ ክልሎች የሚከተሉት ሀላፊነቶች ይኖሯቸዋል፦

- ለአገራዊ ሽግግር ፍትሕ ሂደት አጋዥ የሆኑ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶችን መለየት እና ማሳወቅ፤
- በማካካሻ ትግበራ ሂደት ተጎጂዎችን መለየት፣ ለተጎጂዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ
- ለሽግግር ፍትሕ ሂደት የሚጠቅም መረጃና ማስረጃ ማሰባሰብ፣ አደራጅቶ ማቅረብ፤
- በወንጀል የተሳተፈ ሰውን አሳልፎ መስጠት፣ ጥፋተኞችን ሪፖርት ማድረግ እና ለፍርድ ማቅረብ፣ ፍትሕን ለማረጋገጥ በቅንጅት መሥራት፤
- የሽግግር ፍትሕ ሂደቱን ለማስፈጸም ለሚሳተፉ አካላት ምቹ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት፣ ደህንነታቸውን መጠበቅ፤
- በዚህ ፖሊሲ መሰረት ክልል–አቀፍ ተቋማዊ ማሻሻያዎችን ማከናወን፤
- የሚያስተዳድሩት ህዝብ በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ላይ አመኔታ እንዲኖረው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት፤
- የህዝቦች አብሮነት እና ግንኙነት የሚያጠናክሩ ስራዎችን መስራት፣ ሀሳብ ማመንጨት እና የየክልሉ ህዝብ ተሳታፊነትን ማረጋገጥ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ – 'በአገራዊ የሽግግር ፍትሕ ሂደት የማይሸፈኑ ጉዳዮች፣ ጥሰቶች እና ግጭቶችን' በተመለከተ ክልሎች የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በባለቤትነት ይተገብራሉ፡፡

- 'በአገራዊ የሽግግር ፍትሕ ሂደት የማይሸፈኑ' የዕርቅ እና የማካካሻ ስርዓቶችን ከአገራዊ መርሆችና መስፈርቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ መተግበር፤
- በተመሳሳይ መርሆች ላይ ተመስርተው የእውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና እውቅና የመስጠት ስራዎችን ማከናወን፤
- ለተፈጸሙ በደሎች በመንግስት ደረጃ ይቅርታ መጠየቅ፤
- ለተጎጂዎች የመልሶ ማቋቋም፣ የማገገሚያ፣ የመታሰቢያ እና ማስታወሻ ስርዓቶችን መቅረፅ እና መተግበር፣ የተፈናቀሉ ሰዎችን ወደ አካባቢያቸው እንዲመለሱ ማድረግ እና ሌላ ጥቃት እንዳይደርስባቸው ጥበቃ ማድረግ፥
- በአገር–አቀፍ ደረጃ በሚወጡ መስፈርቶች መሰረት በህጎቻቸው እና ተቋሞቻቸው ላይ ተገቢ ማሻሻያዎችን ማከናወን፤
- በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ የሚሳተፉ የባህል ፍትሕ ሥርዓቶችን ከተቀመጡ መርሆች እና መስፈርቶች አንፃር በመለየት እውቅና መስጠት፣ አሰራራቸውን እና ተጠያቂነታቸውን በህግ በግልፅ መደንገግ፤
- የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ በደሎች እና ቁርሾዎች እንዳይደገሙ ለማድረግ አስፈላጊውን ማድረግ፣ በቅንጅት እና በትብብር መስራት።

## 2.8. በሽግግር ፍትሕ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቶች ሚና

በአገሪቱ ለዘመናት ሲተገበሩ የቆዩ በርካታ ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች አሉ፡፡ በማህበረሰብ ሆነ በግለሰብ ደረጃ የሚከሰቱ የተለያዩ ግጭቶችን በእውነት እና በይቅርታ ላይ የተመሰረተ ፍትሕ የመስጠት፣ ስብራቶችን የመጠገን እና ሰላም የማስፈን ሚና ሲጫወቱ ቆይተዋል፡፡ እነዚህ የባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ የሚጫወቱትን አካባቢያዊ ወይም ሀገራዊ ሚና ለይቶ ጥቅም ላይ ማዋል የሽግግር ፍትሕን ዓላማዎች ለማሳካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡

ስለሆነም ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቶች ያሉባቸውን ክፍተቶች እንዲስተካከሉ በማድረግ በሚተገበረው የሽግግር ፍትሕ ሂደት ከሌሎች የሽግግር ፍትሕ ተቋማት ጋር በመቀናጀት እውነትን በማፈላለግ፣ ዕርቅ በማስፈን፣ በማካካሻ እና በምህረት መስጠት ተግባራት፣ እንዲሁም ማህበረሰባዊ ሰላምን ለማስፈን በሚደረጉ ስራዎች ማእቀፍ ጉልህ ሚና እንዲኖራቸው ይደረጋል።

ከዚህ አንፃር ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች ሥርዓቶችን በተመለከተ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡

- ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቶች ከሌሎች ተቋማት ጋር በመሆን እውነትን በማፈላለግ፣ ተጠያቂዎች ለፍትሕ እንዲቀርቡ በመርዳት፣ በዕርቅ እና በማካካሻ ሥርዓት፣ እና ሌሎች የህዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ለማጠናከር የሚያስችሉ ስራዎችን በመስራት ዋናውን የሽግግር ፍትሕ ሂደት የማገዝ እና የመደገፍ ሚና ይኖራቸዋል፤
- በኮሚሽኑ የሚቀመጡ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ በሽግግር ፍትሕ ስርዓቱ በሚቋቋመው ሀገራዊ የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽን የማይከናወኑ ወይም የማይሸፈኑ ጉዳዮችን፣ ወይም ቀለል ያሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እና ግጭቶችን ለመፍታት እንዲቻል ተቋማቱ በእውነት ማፈላለግ፣ በዕርቅ ተግባራት እና ተያያዥ አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ ይደርጋል፤

- አካባቢያዊ ወይም አገራዊ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቶችን ለመለየት የሚያስችሉ መርሆዎችና መስፈርቶች በግልፅ ይወጣሉ፤
- ተቋማቱ ከፖለቲካ፣ ከዘር፣ ከሀይማኖት፣ ከፆታ እና ሌሎች አድሏዊ አሰራሮች ነፃ እና ገለልተኛ ሆነው ለእውነት እና ለፍትሕ ብቻ የሚሰሩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሥርዓት ይዘረጋል፤
- የተቋማቱ አሰራር የሴቶች እና ህፃናትን ተሳትፎ እና መብት እንዲያከብር ተገቢ ስራ ይሰራል፡፡

## 2.9. የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች (cross-cutting issues)

የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ እና ትግበራ ሂደት አንዱ ገዢ መርህ ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ልዩ ትኩረት መስጠት ነው።

ስለሆነም የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው እና የትግበራ ሂደቱ ልዩ ትኩረት ለሚሹ እና ለጉዳት ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ለሴቶች፣ ለህጻናት፣ ለወጣቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን እና ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ልዩ ፍላጎት እና ጥቅም ትኩረት በሚሰጥ አግባብ ይከናወናሉ።

ልዩ ትኩረት ከሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎች አንፃር የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-

- ፖሊሲውን ለመተግበር የሚወሰዱ የህግ፣ የአሰራር እና የአደረጃጀት እርምጃዎች የሴቶችን ትርጉም ያለው ተሳትፎ እና ውሳኔ ሰጪነት፣ እንዲሁም የሴቶች ተመጣጣኝ ውክልናን በሚያረጋግጥ አግባብ የሚከናወኑበት አሰራር ይዘረጋል፤
- የሽግግር ፍትሕ ሥርዓት ትግበራው በማህበረሰቡ ለዘመናት የቆዩ የተዛቡ የስርአተ–ጾታ አመለካከቶችን እና ተጋላጭነታቸውን በዘላቂነት ለመቀነስ በሚያስችል አግባብ ይከናወናል፤
- የምርመራ እና የክስ ሂደቶች ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች እና ልጃገረዶች ምቹ የሆኑ፣ ክብራቸውን የሚጠብቁ፣ ለዳግም ጉዳት የማያጋልጡ፣ አስፈላጊ የስነልቦና እና የምክር ድጋፎችን የሚያቀርቡ፣ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ የማገገሚያ/መጠለያ አገልግሎትን ያካተቱ እንዲሆን ይደረጋል፤
- የምርመራ እና ክስ፣ እንዲሁም እውነት የማፈላለግ እና የዕርቅ ስራ ሂደቶች የሴቶችን የባህል እና የእምነት ልዩነቶች፣ እንዲሁም የማህበረሰብን ተጽእኖዊ አኗኗር ግምት ውስጥ በማስገባት እና ለተሳትፎ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ይተገበራሉ፤
- በክስ እና ምርመራ ወቅት የሚተገበሩ የሥነ-ሥርዓት እንዲሁም የማስረጃ ህጎች ጾታዊ ጥቃት የፈጸሙ አጥፊዎች ተጠያቂነትን ማረጋገጥ በሚያስችሉ መልኩ ይተገበራሉ፤
- የእውነት ማውጣት ሂደቱ ጾታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች ልዩ ትኩረት ይሰጣል፤ የጥቃቶችን ተከታታይነት (pattern) በማጥናት ምክንያቶቹ ይፋ እንዲወጡ ያደርጋል፤
- የእውነት ማውጣት ሂደቱ በአገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ሌሎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ባካተተ መልኩ ይተገበራል፤
- የሽግግር ፍትሕ ትግበራን አስመልክቶ የሚተላለፉ የማህበረሰብ ግንዛቤ ትምህርቶች እና መግለጫዎች ለሴቶች እና ልጃገረዶች ተደራሽ መሆናቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ ይከናወናሉ፤
- ህጻናትን በተመለከተ ሂደቱ በህገ-መንግስቱ እና በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች ላይ በተቀመጡ መብቶች መሰረት ይተገበራል፤

- የወንጀል ተጠያቂ ህጻናትን በመለየት ሂደት፣ እንዲሁም በምርመራ፣ ክስ፣ ክርክር እና ውሳኔ አሰጣጥ ለህጻናት ተገቢው ትኩረት ይሰጣል፤ ጥንቃቄም ይደረጋል፤
- የሽግግር ፍትሕ ትግበራው የወጣቶችን ትርጉም ያለው ተሳትፎ ባረጋገጠ መልኩ ይከናወናል፤ ለአካል ጉዳተኞች እና ለአረጋውያን ተደራሽ እንዲሁም አካታች የሆኑ አሰራሮችን ያካተተ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የመንግስት እና የባለድርሻ አካላት ሚና እና የክትትል እና ድጋፍ ሥርዓት

### 3.1. የመንግስት አካላት እና ባለድርሻ አካላት ሚና

ከላይ በክፍል ሁለት ላይ የተመለከቱት የሽግግር ፍትሕ ስልቶች አንዱ ሌላውን የሚተካ ሳይሆን እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ እና የሚመጋገቡ ናቸው፡፡ ስለሆነም ስልቶቹን በተቀናጀ መንገድ በመደጋገፍ እና በትብብር እንዲተገበሩ ማድረግ ያስፈልጋል። በፖሊሲው መሰረት የሽግግር ፍትሕ ስራዎችን ተግባራዊ የሚያደርጉ ተቋማት በርከት ያሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ተቋማት እንዲቋቋሙ ሁኔታዎችን ከማመቻቸት አንስቶ ስራቸውን ሙሉ ለሙሉ እስኪጀምሩ ድረስ ድጋፍ የሚያደርጉ ተቋማት ተግባር እና ኃላፊነት በዚህ ፖሊሲ ላይ በግልፅ ሊመላከት ይገባል፡፡

በሌላ በኩል በፖሊሲው መሰረት ተቋቁመው የሽግግር ፍትሕ ስራዎችን ተግባራዊ የሚያደርጉ ተቋማት ስራቸውን ከጀመሩ በኋላም ቢሆን በመካከላቸው የሚኖረውን ቅንጅታዊ አሰራር የሚያመቻች እና የሚመራ መዋቅር እና ድጋፍ የሚያደርጉ ተቋማት ያስፈልጋሉ፡፡

በአጠቃላይ በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ የሚኖረው የመንግስት እና የባለድርሻ አካላት ሚና እንደሚከተለው ቀርቧል።

#### 3.1.1. የመንግስት አካላት ሚና

**ሀ) የፍትሕ ሚኒስቴር**

የፍትሕ ሚኒስቴር የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሥርዓቱን በበላይነት የመምራት እና የማስተባበር ኃላፊነት የተሰጠው ተቋም ነው፡ ፡ የፌዴራል መንግስቱም የሕግ አማካሪ ነው፡፡ ስለሆነም የሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲፈፀም ለማድረግ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን ከመፍጠር አንፃር የፍትሕ ሚኒስቴር የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ይደረጋል፡፡

ይህ ፖሊሲ ተግባራዊ እንዲሆን በማመቻቸት እና በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ የተለያዩ ተግባራትን የሚያከናውኑ አካላትን በመደገፍ ረገድ የፍትሕ ሚኒስቴር የዋና አስተባባሪነት ሚና ይኖረዋል፤በዋናነት ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን ተግባራት ያከናውናል፡-

- በዚህ ፖሊሲ የተለያዩ የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቋቋሙ የተመለከቱ ተቋማት ማቋቋሚያ የሕግ ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤
- የሚቋቋሙ ተቋማት ራሳቸውን ችለው ስራ እስኪጀምሩ ድረስ የውስጥ አሰራር ደንቦችን እና መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤ በተያያዥ ጉዳዮች ላይ ተገቢው ድጋፍ ያደርጋል፤
- የተለያዩ የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን ተግባራዊ በሚያደርጉ ተቋማት እና አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር ያደርጋል፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ፖሊሲውን የማስተዋወቅ እና ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ይሰራል፥ አጠቃላይ የሽግግር ፍትሕ አፈፃፀምን ይከታተላል፤ ይህን የሚያከናውን ከሚመለከታቸው ተቋማት እና ሲቪል ማህበረሰብ ተወካዮች

Office of the Prime Minister

የተውጣጡ አባላት ያሉት አንድ አደረጃጀት ይመሰርታል፤ ለዚህ የሚሆን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ የአሰራር ሥርዓቶቹ በአግባቡ ተግባራዊ እንዲሆኑ አስፈላጊ ድጋፍ ያደርጋል።

**ለ) የገንዘብ ሚኒስቴር**

የገንዘብ ሚኒስቴር የአገሪቱን የፋይናንስ ሥርዓት የማስተዳደር፣ የፌዴራል መንግስት በጀትን የማዘጋጀት፣ የተፈቀደ በጀትን ለሚመለከተው አካል የመላክ፣ አፈጻጸሙን የመገምገም እና የመሳሰሉት ተግባራት እና ኃላፊነቶች ያሉት መስሪያ ቤት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከሽግግር ፍትሕ ሥርዓት ትግበራ ጋር በተያያዘ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

- በአገር አቀፍ ደረጃ የሽግግር ፍትሕ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል በቂ በጀት ይመድባል፤
- የሽግግር ፍትሕ የተለያዩ ክፍሎችን ተግባራዊ ለሚያደርጉ ልዩ ተቋማት/አካላት ስራቸውን ለማከናወን የሚበቃ በጀት ይመድባል፣ ያስተላልፋል፤
- በተቋማቱ ማቋቋሚያ ህግ ላይ በሚመለከተው አግባብ በጀት ጥቅም ላይ የሚውልበትን ልዩ አሰራር ያሳልጣል፤
- የሽግግር ፍትሕ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የገንዘብ እና የአይነት ድጋፍ ማግኘት እንዲቻል ከተለያዩ ዓለም አቀፍ እና አገር አቀፍ አጋር አካላት ጋር በቅርበት ይሰራል፤ ሀብት ያሰባስባል፤ የሚገኘውን የገንዘብ ድጋፍ በአግባቡ ማስተዳደር እና መጠቀም የሚቻልበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

**ሐ) ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን**

የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚተገበሩ የአደረጃጀት ጥናቶችን ትክክለኛነት እና አግባብነት መርምሮ ውሳኔ የመስጠት፣ በውሳኔው መሠረት ተግባራዊ መሆኑን የመቆጣጠር፣ የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች ስምሪት በብቃት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የማድረግ፣ ብቃት ያላቸው የሥራ መሪዎች እና ባለሙያዎችን ወደ መንግስት መስሪያ ቤቶች ለመሳብና ለማቆየት የሚያስችል የክፍያ ሥርዓት የመመስረት ኃላፊነት የተሰጠው የመንግስት ተቋም ነው፡፡

በመሆኑም ከሽግግር ፍትሕ አተገባበር ጋር በተያያዘ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

- የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የተቋቋሙ ተቋማትን በተመለከተ በተቋማቱ ማቋቋሚያ ህግ ላይ በሚመለከተው አግባብ የተልዕኳቸውን ልዩ ባህርይ ግምት ውስጥ ያስገባ አደረጃጀት እንዲኖራቸው እገዛ ማድረግ፤
- የተቋማቱ አደረጃጀት የተሻለ እውቀት እና ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎችን ለመቅጠር ወይም ለመመደብ የሚያስችል የደመወዝ እና የጥቅማጥቅም ማዕቀፍ እንዲሆን እገዛ ማድረግ፤
- ተቋማቱ በተቻለ ፍጥነት የሰው ሀይል እንዲሟላላቸው የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን።

**መ ) የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን**

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ባለስልጣን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የመመዝገብ፣ የመደገፍ፣ ሥራቸውን የማሳለጥ እና የማስተባበር፣ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን የማከናወን እና መሰል ተግባራት እና ኃላፊነቶች ያሉት የመንግስት ተቋም ነው፡፡

ባለስልጣኑ ከሽግግር ፍትሕ ሥርዓት አተገባበር ጋር በተያያዘ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

- የሽግግር ፍትሕ ስርዓቱ አተገባበር በህዝብ ተቀባይነት እንዲኖረው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ማህበረሰቡን የማሳወቅ እና የማንቃት ስራ እንዲሰሩ ማስተባበር፤

- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍልን የሚወክሉ/ያቀፉ እንደመሆናቸው መጠን እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች በሽግግር ፍትሕ ሥርዓት አተገባበር ሂደት በንቃት ይሳተፉ ዘንድ እንዲያበረታቱ ማድረግ፤
- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሽግግር ፍትሕ አተገባበር የቴክኒክ እና የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያደርጉ ማስተባበር፡፡

**ሠ) የፌዴራል እና የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች**

የፌዴራል እና የክልል ፖሊስ ተቋማት የማህበረሰቡን ሰላም እና ደህንነት የማስጠበቅ ተግባር እና ኃላፊነት ያላቸው መንግስታዊ ተቋማት ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ ከሽግግር ፍትሕ ሥርዓት አተገባበር ጋር በተያያዘ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች አሏቸው፡-

- የተለያዩ የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚቋቋሙ ተቋማት ወይም አደረጃጀቶች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ የሰላም እና የፀጥታ ችግር እንዳይገጥማቸው አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ፤
- የሽግግር ፍትሕ ሥርዓት የተለያዩ ክፍሎችን ተግባራዊ ለማድረግ በልዩ ሁኔታ ጥበቃ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይህን ማከናወን።

**ረ) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት**

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አዋጆችን የማውጣት፣ የተቋማትን የስራ አፈፃፀም የመገምገም እና የህብረተሰብ ጥያቄ ለመንግስት እንዲቀርብ እና መፍትሄ እንዲያገኝ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት አካል ነው፡፡

ከሽግግር ፍትሕ አተገባበር ጋር በተያያዘ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

- የተለያዩ የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ሕጎችን ቅድሚያ እና ትኩረት በመስጠት ያፀድቃል፤
- ለሽግግር ፍትሕ ስርአቱ ትግበራ የሚቋቋሙ ተቋማት ኮምሽነሮች እና ዳኞች ሹመት ግልፅ በሆነ እና የህዝብን ተሳትፎ በሚያረጋግጥ ሂደት እንዲከናወን ያደርጋል፤
- የሽግግር ፍትሕ አጠቃላይ ስርአት የህዝብን አመኔታን ባረጋገጠ መንገድ፣ በታቀደው እና በታሰበው አግባብ እየተተገበረ ስለመሆኑ ተገቢ ክትትል ያደርጋል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤ አስፈላጊውን በጀት ያፀድቃል፤
- የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን ተግባራዊ የሚያደርጉ ተቋማት ስራቸውን በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ይሰጣል።

**ሰ) የሰላም ሚኒስቴር**

የሰላም ሚኒስቴር ከሽግግር ፍትሕ ሥርዓት አተገባበር ጋር በተያያዘ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

- የሽግግር ፍትህ አተገባበርን አስመልክቶ ሀገራዊ መግባባት እንዲፈጠር እና አዎንታዊ ሰላም እንዲገነባ ከፍትህ ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአቅም ግንባታ ስራ ይሰራል፤
- ዘላቂ ሰላምን ከማረጋገጥ አኳያ በዚህ ፖሊሲ አተገባበር ወቅት በክልሎች እና ፌዴራልመንግስቱ መካከል እንዲሁም በክልሎች መካከል ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር ድጋፍ ያደርጋል፥
- የሽግግር ፍትህ ዘላቂ ሰላምን ሊያመጣ በሚችል አግባብ በሁሉም ክልሎች ወጥ በሆነ መንገድ እየተተገበረ ስለመሆኑ ይከታተላል፥ ድጋፍ ያደርጋል፥

- በእርቅና በምህረት የተስተናገዱ ጉዳዮች በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ እንዲችሉ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ የደርጋል፥
- የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፥ በሽግግር ፍትህ ሂደት ውስጥ በአግባቡ መስተናገዳቸውን፥ ወደ ቦታቸው መመለሳቸውን እና መሰል መብቶች የተጠበቁላቸው ስለመሆኑ ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል፤
- የሽግግር ፍትህ አተገባበር በሀገሪቱ ዘላቂ አዎንታዊ ሰላምን ለማስፈን በሚያስችል መልኩ እንዲሆን ይሰራል።

**ሸ) የሴቶች እና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር**

- በፖሊሲው ልዩ ትኩረት ለሚሹ የሕብረተሰብ ክፍሎች በተመለከተ የተቀመጡ አቅጣጫዎች መፈጸማቸውን ይከታተላል፤ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤
  በተለይ ከጾታዊ ጥቃት ጋር በተያያዘ አስፈላጊ የሆኑ የስነልቦናና የምክር ድጋፎች እንዲሁም የማገገሚያ አገልግሎት ለተጎጂዎች ተደራሽ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
  የሽግግር ፍትሕ ትግበራን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአቅም ግንባታ ስራዎች ልዩ ትኩረት ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

**ቀ) የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት**

ከሽግግር ፍትህ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለሀገርና ለትውልድ በአስተማሪነትና በቅርስነት ሊያገለግል በሚችልበት አግባብ አደራጅቶ በማያዝና ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ ሐላፊነት አለው።

**በ) ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት**

የሽግግር ፍትሕን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ሙያዊ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ባለሙያዎች በሂደቱ የሚሳተፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤የግንዘቤ እና የአቅም ግንባታ ስራዎችን መደገፍ እና ተግባራዊ ማድረግ

የሽግግር ፍትሕን በመተግበር ሂደት የሚሳተፉ ተቋማት ለሚያከናውኑት ተግባራት የሚያግዝ የጥናት እና የምርምር ስራዎችን ማከናወን

**ተ) የሌሎች የመንግስት ተቋማት ሚና**

ከሽግግር ፍትሕ ሥርዓት አተገባበር ጋር በተያያዘ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ሚና የሚኖራቸው አካላት ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል፣ በተለይም የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚቋቋሙ ወይም የሚደራጁ ተቋማት ሊያጋጥማቸው የሚችል የሰው ሀይል፣ የበጀት እና ሌሎች መሰል ጉዳዮችን ለመቅረፍ የሚያስችል እገዛ ማድረግ አለባቸው፡፡

### 3.1.2. የባለድርሻ አካላት ሚና

**ሀ) የኢትዮጵያ ሰብዐዊ መብቶች ኮሚሽን**

የሽግግር ፍትሕ ሒደት ትግበራው የሰብዐዊ መብት ድንጋጌዎችን ያከበረ፣ ተጎጂን ማዕከል ያደረገ እና የፖሊሲውን መርሆዎች ያከበረ መሆኑን ይከታተላል፤ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

**ለ) የኢትዮጵያ አገራዊ የምክክር ኮሚሽን**

የሽግግር ፍትሕ የትግበራ ሂደት እና አገራዊ ምክክሩ ተመጋጋቢ በሆነ መልኩ ተግበራዊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፡፡

### ሐ) የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጥቅሞች/መብቶች የሚወክሉ ተቋማት ናቸው፡፡ ስለሆነም ድርጅቶቹ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ስለ ሽግግር ፍትሕ ሥርዓት እና ሂደት በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የማስገንዘብ፣ የማሳወቅ እና አገራዊ ንቅናቄዎችን በመፍጠር ህዝቡ በሙሉ የባለቤትነት ስሜት እንዲሳተፍ የሚያስችለው ስራ እንዲሰሩ ይደረጋል።

በተጨማሪም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሽግግር ፍትሕ ሂደት አተገባበር ወቅት በቀጥታ እና በንቃት እንዲሳተፉ፣ ሂደቱን እንዲደግፉ እና እንደአግባብነቱም የሂደቱን ውስን ክፍሎች በሙሉ ሀላፊነት የሚያስፈፅሙበት አውድ ይፈጠራል፡፡ በዚህ ረገድ በተለይ አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሙሉ የባለቤትነት ስሜት እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡ ዓለማቀፍ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችም እንደአግባብነቱ ከአገር አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት ወይም በተናጠል የህዝብ ባለቤትነት እና የአገር መሪነት መርህን በሚያከብር አውድ በሂደቱ ትግበራ የሚሳተፉበት ስርአት ይዘረጋል፤ ስርአቱን በፋይናንስ፣ በቴክኒክ እና ሌሎች መንገዶች የሚደግፉበት አሰራር ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

### መ) የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት

ምክር ቤቱ ከሽግግር ፍትሕ ሥርዓት አተገባበር ጋር በተያያዘ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

- የሽግግር ፍትሕ ስርዓቱ አተገባበር በህዝብ ተቀባይነት እንዲኖረው የፖለቲካ ፓርቲዎች ማህበረሰቡን የማሳወቅ እና የማንቃት ስራ እንዲሰሩ ማስተባበር፤
- የፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍልን የሚወክሉ/ያቀፉ እንደመሆናቸው መጠን እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች በሽግግር ፍትሕ ሥርዓት አተገባበር ሂደት በንቃት ይሳተፉ ዘንድ እንዲያበረታቱ ማድረግ፤

### ሠ) የፖለቲካ ፓርቲዎች

የፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጥቅሞች/መብቶች የሚወክሉ ተቋማት ናቸው፡፡ ስለሆነም ፓርቲዎቹ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ስለ ሽግግር ፍትሕ ሥርዓት እና ሂደት በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የማስገንዘብ፣ የማሳወቅ እና አገራዊ ንቅናቄዎችን በመፍጠር ህዝቡ በሙሉ የባለቤትነት ስሜት እንዲሳተፍ የሚያስችለው ስራ እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

### ረ) የሌሎች ባለድርሻ አካላት ሚና

ከሽግግር ፍትሕ ሥርዓት አተገባበር ጋር በተያያዘ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ሚና የሚኖራቸው አካላት ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል። በተለይም የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚቋቋሙ ወይም የሚደራጁ ተቋማት ሊያጋጥማቸው የሚችል የበጀት እና ሌሎች መሰል ጉዳዮችን ለመቅረፍ የሚያስችል እገዛ ማድረግ አለባቸው፡፡

## 3.2. የፖሊሲው አፈፃፀም፡ ክትትል እና ድጋፍ ሥርዓት

ይህ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ በሚፈለገው አግባብ ተግባራዊ እንዲሆን ራሱን የቻለ የክትትል እና ድጋፍ ሥርዓት ሊኖረው ይገባል:: በዚህ ፖሊሲ ላይ የተመለከቱ ተቋማት እና አደረጃጀቶች ተቋቁመው እና ተደራጅተው ስራቸውን እስኪጀምሩ ድረስ፣ እንዲሁም ስራቸውን ከጀመሩ በኋላም ውጤታማ ሆነው እንዲቀጥሉ ለማድረግ የተቀናጀ እና የተናበበ ድጋፍ እና ክትትል የሚካሄድበት ስርአት መኖር አለበት።

ከላይ በክፍል 3.1.1 ለፍትሕ ሚኒስቴር የተሰጠው ቅንጅታዊ አሰራር የመመስረት እና ለዚህ የሚሆን የባለ–ብዙ ተቋማት እና ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አደረጃጀት መፈጠሩ እንደተጠበቀ ሆኖ – ፖሊሲው በትክክል ወደ መሬት ወርዶ ተግባራዊ የሚሆንበትን ዝርዝር አካሄድ የሚመራ 'የፖሊሲ አፈፃፀም ፍኖተ ካርታ' ይዘጋጃል። ፍኖተ ካርታው ፖሊሲው ከጸደቀ በኋላ የሚከናወኑ ተግባራት በዝርዝር ምን ምን እንደሆኑ፣ ቅደም ተከተላቸውን፣ መቼ እንደሚከናወኑ፣ ማን እንደሚያከናውናቸው እና በዚህ ፖሊሲ ላይ የተመለከቱ አካላት ተግባር እና ኃላፊነት ምን እንደሆነ የሚያመላክት ይሆናል። የፍትሕ ሚኒስቴር የሚያቋቁመው የክትትል አደረጃጀትም ይህን ፖሊሲ እና ፍኖተ ካርታውን መነሻ በማድረግ የየተቋማቱ ተግባራት በአግባቡ እና ቅንጅታዊ አሰራርን መሰረት በማድረግ ይፈፀሙ ዘንድ በቋሚነት የክትትል እና ድጋፍ ስራ የሚሰራ ይሆናል።